# አዲስ ዘመን

እንድ

ሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 233 ሚያዝያ 23 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# የአቶ ግርማ የሺጥላ የቀብር ሥነ-ሥርዓት በመሐል ሜዳ ተፈጸመ



ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባል የነበሩት አቶ ግርማ የሺጥላ የቀብር ሥነ-ሥርዓት በትናትናው እለት በመሐል ሜዳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

የሰሜን ሸዋ ዞን ዋና አስተዳደሪ አቶ መካሻ ዓለማየሁ በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ አቶ ግርማ በጣም ደፋር፣ ፊት ለፊት ተናጋሪ ላመነበት ሀሳብ የማይታጠፍ ጀግና እና የቁርጥ ቀን ልጅ ነበር። ግርማ አስተዋይና በሳል፣ ሀሳቡ ተቀድቶ የማያልቅ፣ በሰሜን ሸዋ ያሉ መሪዎችን ኮትኩቶ ለወግ ለማዕረግ ያበቃ፣ በአማራ ክልል ሁለንተናዊ ለውጥ ያመጣ


የአቶ ግርማ የሺጥላ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


1967 - 2015 ዓ.ም



"ጽንፈኝነት የአማራ ክልል ሕዝብ ላይ የተቃጣ አደገኛ የመከራ በትር ነው"

-ዶክተር ይልቃል ከፋለ
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር


ገጽ 4




"የወንድማችንን ገዳዮች መንግሥትና ሕዝብ በመረባረብ ለፍርድ እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለን"

- አቶ ኃይሌ የሺጥላ
የአቶ ግርማ የሺጥላ ወንድም


ገጽ 4




ፎቶ - ዳኜ አበራ

# የብልጽግና ጉዞ በሴቦችና በጽንፈኞች አይደናቀፍም

አዲስ አበባ፡- የብልጽግና ጉዞ በሌቦችና በጽንፈኞች የማይደናቀፍ መሆኑን እናረጋግጣለን ሲሉ የአቶ ግርማ የሺጥላ የአስከሬን ሽኝት ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙት የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ተናገሩ።

አቶ አደም ፋራህ በዚሁ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት በአቶ በግርማ የሺጥላ ላይ በተፈጸመው ዘግናኝ ግድያ የተሰማቸውን መራር ኃዘን በራሳቸውና በፓርቲያቸው ስም ገልጸዋል።

ለአቶ ግርማ ቤተሰቦች፣ ለአማራ ክልል ሕዝብ፣ ለብልጽግና ፓርቲ አባላትና አመራሮች እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከአቶ ግርማ የሺጥላ ጋር ለተሰዉ ወገኖች ቤተሰቦችም በተመሳሳይ ፈጣሪ መጽናናትን እንዲሰጣቸው ተመኝተዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ለሀገር፣ ለሕዝብና ለፓርቲው ያበረከተውን የላቀ አስተዋፅኦ መቼም አንረሳውም ያሉት


የብልጽግና ጉዞ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

















ዜና

# ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በማፍረስ ክልላዊ ሥልጣን ለመያዝ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ 47 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን የጋራ ግብረ ኃይሉ አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በማፍረስ ክልላዊ ሥልጣንን በኃይል ለመያዝ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት በህቡዕ ተደራጅተውና ተቀናጅተው በሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች ላይ የማያዳግም ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በገባው ቃል መሠረት ርምጃ እየወሰደ መሆኑን አስታወቀ።

በመሆኑም የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ- ኃይል እየወሰደ ባለው እርምጃ በዚህ ህቡዕ አደረጃጀት ውስጥ ሲንቀሳቀሱና የሽብር ተግባር ሲፈጽሙ የተገኙ 47 ተጠርጣሪዎችን ከበርካታ የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያዎች፣ ቦንቦችና ተቀጣጣይ ፈንጂዎች እንዲሁም ከሳተላይት መገናኛ መሣሪያዎች እና የተለያዩ መረጃዎችን ከያዙ ላፕቶፖች ጋር በቁጥጥር ሥር ማዋሉን ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ አመልክቷል።

ተጠርጣሪዎቹ የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮችን የግድያ ዒላማ በማድረግ፤ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል በመናድ የክልሉን መንግሥታዊ መዋቅር በመቆጣጠር የፌደራል መንግሥትን ለመጣል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተደራጅተው እና ተቀናጅተው በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ እንደተደረሰባቸው አስታውቋል።

ግብረ-ኃይሉ ለኢፕድ በላከው መግለጫ፤ መንግሥት የዴሞክራሲ ምሕዳሩን ለማስፋት እና ለሐሳብ ትግል ሰፊ ዕድል በመስጠቱ እንዲሁም ችግሮች በውይይት እንዲፈቱ ባደረገው ጥረት ብዙዎች ይሄንን ዕድል መጠቀማቸውን አስታውሷል። ይሁንና የአማራን ሕዝብ የማይወክሉ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች የመንግሥትን ሰላማዊ አማራጭ በመግፋት በውጭ ከሚገኙ ግብረ-አበሮቻቸው ጋር በህቡዕ በመገናኘት የፖለቲካ፣ የወታደራዊ፣ የኢንተለጀንስ፣ የሚዲያ እና የፋይናንስ ክንፍ ማቋቋማቸው እንደተደረሰበት መግለጫው አመልክቷል።

የጋራ ግብረ-ኃይሉ መግለጫ እንዳመለከተው፤ የጽንፈኛ ኃይሎችን የፖለቲካ፣ የወታደራዊ፣ የኢንተለጀንስ፣ የፋይናንስ እና የሚዲያ ክንፍ የሚመራው ዶ/ር ወንድወሰን አሰፋ የተባለ ግለሰብ ሲሆን፤ ይህ ክንፍ በተለያዩ የውጭ ሀገራት ከሚገኙ 16 ጽንፈኛ የዲያስፖራ አባላት ጋር ትስስር በመፍጠር በሚያገኛቸው የሎጀስቲክስ እና የፋይናንስ ድጋፎች በአማራ ክልል ከባህርዳር ከተማ ጀምሮ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ታጣቂዎችን የመመልመል፣ የማሰልጠን፣ የማስታጠቅና የማሰማራት ተግባር በማከናወን በክልልና በፌደራል ደረጃ ሽብር እና ግድያ እንዲፈጽሙ ተልዕኮ ሲሰጥ እንደነበር በተደረገ ክትትል እና ምርመራ ተደርሶበታል ብሏል መግለጫው።

ለዚህም በለጠ ሺጋው እና ምሕረት ወዳጀ ወይም በቅጽል ስሙ ምሬ ወዳጆ በተባሉት የጽንፈኛ ኃይሉ ታጣቂ መሪዎች እና ግብረ-አበሮቻቸው ሰሞኑን በትውልድ ቀዬአቸው ግፍና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን የተገደሉት የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ እና የጥቃት ሰለባ የሆኑ የሥራ ባልደረቦቻቸው ማሳያ ናቸው ብሏል የጋራ ግብረ-ኃይሉ መግለጫ።

የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል መግለጫ አክሎም፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የሚገኙ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች በፈጠሩት ህቡዕ አደረጃጀት እኩይ ዓላማቸውን ለማስፈጸም በአማራና በሌሎች አካባቢዎች በሚገኙ 130 ወረዳዎች የመለመላቸውንና በህቡዕ ያዘጋጇቸውን 450 ግለሰቦች የአማራ ክልል ሕዝብ የመረጣቸውንና በተለያዩ የአመራር እርከኖች ላይ ያስቀመጣቸውን በኃይል በማስወገድ በራሳቸው መዋቅር የመተካት ሥራ ሲሠሩ እንደነበር በክትትል እና በምርመራ የተደረሰባቸው መሆኑን አስታውቋል።በተጨማሪም ጽንፈኛ ኃይሎች የክልሉን የፀጥታ ኃይልንም በራሳቸው ታጣቂዎች ለመቀየር ተዘጋጅተው እንደነበር የተገኘው መረጃ ማመላከቱን ገልጿል።

ዶ/ር መሥፍን ኃ/ማርያም፣ ዶ/ር ግሩም ላቀውና ሌሎችም በተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚኖሩ የጽንፈኛ ኃይሉ ተባባሪዎች ከውጭ ሆነው የፖለቲካ ክንፉን እንደሚያስተባብሩ፤ አንተነህ ብርሃን፣ ወርቁ ጓዴና ሌሎችም ከሀገር ውስጥና ከውጭ የሚላከውን ገንዘብ እንዲቀበሉና ለሽብር ተልዕኮ ማስፈፀሚያ እንዲያውሉ የባንክ አካውንት እንደተከፈተላቸው በክትትልና በተደረገው ምርመራ መረጋገጡን የገለፀው የጋራ ግብረ-ኃይሉ መግለጫ፤ ቴዎድሮስ አስፋውን ጨምሮ ሌሎችም በዚሁ የሽብር እንቅስቃሴ ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን መግለጫው አስታውቋል።

መግለጫው አያይዞም የእነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎችን የሚዲያና ፕሮፓጋንዳ ክንፍ የሚመራው መስከረም አበራ በተባለች ግለሰብ መሆኑን ጠቅሶ፤ በዚህ ህቡዕ አደረጃጀት ውስጥ ከሀገር ውስጥ ዳዊት በጋሻው የተባለ ግለሰብ እንዲሁም ከተለያዩ የውጭ ሀገራት ደግሞ ከኢትዮ 360 እና መረጃ ቲቪ ሀብታሙ አያሌው፣ ምንአላቸው ስማቸው፣ ብሩክ ይባስ እና እየሩሳሌም ተ/ፃዲቅ በተጨማሪም ዘመድኩን በቀለ እና ልደቱ አያሌው ከአንከር ሚዲያ መሳይ መኮንን እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦች የዚህ እኩይ ዓላማ አስፈፃሚ አባላት መሆናቸውን በምርመራ መረጋገጡን ገልጿል።

እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች የሐሰት ወሬዎችን በመፍጠር እና ከፍተኛ የሽብር ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ሕዝቡን በብሔር እና በሀይማኖት በመከፋፈልና በማጋጨት የክልል እና የፌደራል መንግሥትን በኃይል ለመጣል እንዲሁም ሀገሪቱ ከጀመረችው የለውጥና የልማት መንገድ ወጥታ ወደ ለየለት ሁከትና ትርምስ እንድትገባ በህቡዕ ተደራጅተው እየሠሩ መሆናቸውን የገለፀው የጋራ ግብረ ኃይሉ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሆነው በሀሰት ሀገር ለማፍረስ የሚሰሩ እነዚህን ጨምሮ ሌሎችም በህቡዕ አደረጃጀቱ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችም ጭምር በሽብርተኝነት ምርመራ እየተጣራባቸው መሆኑን መግለጫው አመልክቷል።

እነዚህ የሽብር ኃይሎች ከሚኖሩባቸው ሀገራት በዓለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅት (ኢንተርፖል) እንዲሁም እነሱ ከሚኖሩባቸው ሀገራት መንግሥት የፀጥታ እና የደኅንነት ተቋማት ጋር በተመሠረቱ የትብብር ማዕቀፎች አማካኝነት ወደ ሀገር ቤት ተላልፈው እንዲሰጡ በሕግም እንዲጠየቁ እየሠራ መሆኑን እና ይህንኑ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጿል።

የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል መግለጫ አክሎም፤ እነዚህ ውጭ ሀገር የሚኖሩ ተፈላጊዎች ከውጭ ሀገር በሚያገኙት እና በሀገር ውስጥ ያላቸውን ሀብት ተጠቅመው ለዚህ እኩይ ተግባር እያዋሉ መሆኑን በምርመራ የተደረሰበት ስለሆነ በሀገር ውስጥ ያላቸውን ሀብት የመለየት እና በህግ የመቆጣጠር ስራ እየተሰራ መሆኑንም ጭምር አስታውቋል።

ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ እየተንቀሳቀሱ የነበሩ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች የኢትዮጵያን አንድነት ከማይፈልጉ የውጭ ፀረ ሰላም ኃይሎች ጋር ተቀናጅተው መንግሥትን በኃይል ለማስወገድ ሲሠሩ በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተጣራባቸው የሚገኝ መሆኑን ያመለከተው የጋራ ግብረ ኃይሉ መግለጫ፤ ኅብረተሰቡ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚወሰደውን እርምጃ ከትጥቅ ማስፈታት ጋር በማያያዝ ውዥንብር ለመፍጠርና የተሳሳተ መረጃ ለማሰራጨት ከሚጥሩ አካላት ራሱን እንዲጠብቅ በጋራ እንዲታገል ጥሪ አቅርቧል።

በመጨረሻም የተጀመረው ሕጋዊ ኦፕሬሽን ከግቡ እንዲደርስ ኅብረተሰቡ እያደረገ ላለው ከፍተኛ ተሳትፎ የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል ምስጋና እያቀረበ፤ በህግ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ጥብቅ ክትትል እየተደረገባቸው ያሉ ተፈላጊዎችን ካሉበት ጠቁሞ እንዲያሲዝም ጥሪ አቅርቧል።



አቶ እዮብ ከበደ

## አዋኪ ድርጊቶችን በፈፀሙ 2 ሺህ 625 የንግድ ቤቶች ላይ ርምጃ ተወሰደ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የተለያዩ ስፍራዎች አዋኪ ድርጊቶችን በፈፀሙ 2 ሺህ 625 የንግድ ቤቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በመተባበር የሆቴል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዓለም አቀፍ ፕሮቶኮልን ጠብቀው እንዲሠሩ የሚያስችል ውይይት ተካሄዷል።

በወቅቱ የባለሥልጣኑ የቁጥጥርና ርምጃ አወሳሰድ ዳይሬክተር አቶ እዮብ ከበደ እንደገለጹት፤ በ2015 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በተደረጉ የቁጥጥር ሥራዎች አዋኪ ድርጊቶችን በፈፀሙ 2 ሺህ 662 የንግድ ቤቶች ላይ ርምጃ ተወስዷል።

በአዋኪ ድርጊቶች ላይ የተሳተፉና ርምጃ የተወሰደባቸው ንግድ ቤቶች በትምህርት ቤቶች 200 ሜትር ውስጥ ሺሻ በማስጨስ፣ ጫት በማስቃምና የሌሊት ጭፈራ ቤቶችን በመክፈት አካባቢውን ሲያውኩ እንደነበሩ አስታውሰዋል።

በትምህርት ቤቶች አካባቢ ሺሻና ጫት ቤት በመክፈት እንዲሁም የቀንና የሌሊት ጭፈራ ቤቶች ከፍተው አዋኪ ድርጊት የፈጸሙ እያንዳንዳቸው የ10 ሺህ ብር ቅጣት ተጥሎባቸዋል። በተጨማሪ ጫት ቤት የከፈቱት ደግሞ እያንዳንዳቸው የአምስት ሺህ ብር ቅጣት ተላልፎባቸዋል ብለዋል።

በተጨማሪም የንግድ ፍቃድ የሌላቸው ቤቶችን ከንግድ ቢሮ ጋር በመተባበር እስከ ማሸግ እና የንግድ ፍቃድ እስከመከልከል የደረሱ ርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረጉን ጠቁመዋል።

ባለሥልጣኑ ከተለያዩ ባለድርሻ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ከግንዛቤ ሥራዎች ጎን ለጎን በአዋጅ ቁጥር 74/2014 እና ደንብ ቁጥር 150/2015 መሠረት ጥብቅ ርምጃ የሚጥሉ የቁጥጥር እና የመከላከል ሥራዎች እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ አዋኪ ድርጊቶችን በፈጸሙ 3ሺ476 ቤቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን ያስታወሱት አቶ እዮብ፤ በ2015 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት የተከናወኑ የቁጥጥርና ርምጃ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

# በመዲናዋ ሕግ በተላለፉ ከ17 ሺ በላይ አሽከርካሪዎች ላይ ርምጃ ተወሰደ - 211 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸው አልፏል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ የፍጥነት ወሰን በጣሱ ከ17 ሺ በላይ አሽከርካሪዎች ላይ ርምጃ መወሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ደህንነት ምክር ቤት አስታወቀ። 211 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ሕይወታቸው ማለፉንም አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ደህንነት ምክር ቤት የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የስድስት ወራት የእቅድ አፈጻጸም መድረክ ሰሞኑን ሲያካሄድ፤ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ክበበው ሚደቅሳ እንደተናገሩት ፤የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅንት ኤጀንሲ ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ እና አጋር አካላት ጋር በመሆን በመዲናዋ በተመረጡ በ30 መንገዶች ላይ በተደረገ ክትትል 17 ሺ 759 አሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን በመጣስ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

በተጨማሪም 211 ሰዎች በመንገድ ትራፊክ አደጋ ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን ከነዚህም 78 በመቶ ወንዶች መሆናቸውንና እድሜያቸውም ከ20 እስከ 49 ውስጥ የሚሆኑ አምራች ዜጎች ናቸው ብለዋል። እንዲሁም 911 ሰዎች ከባድ የአካል ጉዳትና 7 መቶ 49 ቀላል የአካል ጉዳት መድረሱንና ከዚህም ውስጥ 80 በመቶ የሚሆነው ተጎጂ እግረኛ እንደሆነ ተናግረዋል።

በግማሽ ዓመቱ ከቁጥጥር ሥራ ጋር ተያይዞ በተሠራ ሥራ ከተደረገው 17 ሺ 747 የትንፋሽ መሣሪያ ፍተሻ 294 አሽከርካሪዎች ጠጥቶ በማሽከርከር፣ 2 ሺ 698



አቶ ክበበው ሚደቅሳ

የደህንነት ቀበቶ ባለማሰር፣ 213 የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች ሄልሜት ባለማድረግ፣ 4ሺ 818 ስልክ እያናገሩ በማሽርከር፤ እንዲሁም 830 አሽከርካሪዎች በትራፊክ መብራትና አደባባይ ላይ ሕገወጥ ንግድ ሲፈጽሙና ምጽዋት ሲሰጡ በመገኘታቸው እርምጃ እንደተወሰደባቸው ተናግረዋል።

ከነዚህም 575 ሺ 288 አሽከርካሪዎች የኤሌትሮኒክስ አደጋ መመዝገቢያ የሲስተም አማራጮችን በመጠቀም ቅጣታቸውን በሲቢኢ፣ ቴሌብር፣ ሲቢኢ እና የመሳሰሉት አማራጮችን እንዲከፍሉ ተደርጓል ሲሉም ተናግረዋል።

አቶ ክበበው በተጨማሪም በከተማዋ ብልሽት ለደረሰባቸው 84 የመንገድ መብራት እድሳት የተደረገ ሲሆን ሦስት አዳዲስ የትራፊክ መብራት ተተክሏል፣ ለ80 አዲስ የፓርኪንግ ፍቃድ ማረጋገጫ ለማስጠት ታቅዶ ለ71 ፓርኪንግ ፍቃድ ተሰጥቷል፤ ለ41 እድሳት ተደርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

እንዲሁም 57 የፍጥነት ማብረጃ ጉብታና ማንቂያዎች፣ 2ነጥብ9 ኪሜ የኮብልስቶን መንገድ ጥገና፣ 358 ትራፊክ ፍሰትን የሚያጨናንቁ ቁሳቁሶችን የማንሳት፣ እንዲሁም ከ5 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት እንደተከናወነ አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ምትኩ አማረ በበኩላቸው በከተማዋ ከፍተኛ ሕዝብ ቁጥር መጨመር እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት የትራፊክ እንቅስቃሴ ለመጨመር ዋነኛ ምክንያት ነው። ያለውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በከተማ አስተዳደር ከ2019 ጀምሮ የ13 ዓመት የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ በመንደፍና ምክር ቤት በማቋቋም የትራፊክ አደጋ እና የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የትራፊክ አደጋ ለተወሰነ አካል የሚሰጥ ኃላፊነት ሳይሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲሁም መላው ኅብረተሰብ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ተናግረው ተቋማቸውም የተሻለ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር እንደሚሠራ ተናግረዋል።

# የግርማን ሕያውነት የምናረጋግጠው ለሕዝብ የላቀ ጥቅም በመትጋት ነው ሲሉ የቅርብ ወዳጆቹ ተናገሩ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አቶ ሞገስ ባልቻ



አቶ ፍቃዱ ተሰማ



ዶክተር ሰማ ጥሩነህ

አዲስ አበባ፡- የአቶ ግርማ የሺጥላን ሕያውነት የምናረጋግጠው ለሕዝብ የላቀ ጥቅም በመትጋት ነው ሲሉ የቅርብ የሥራ ባልደረሰቦቹና ወዳጆቹ ተናገሩ። ግርማ በባሕሪው ተጫዋች፣ ያዘነን የሚያጽናና ጨለማ የሚመስሉ ጉዳዮችን የሚፈታና ወደ ደስታ የሚቀይር መልካም አሳቢ ሰው እንደነበርም ገልጸዋል።

የአቶ ግርማ የሺጥላ የቅርብ ወዳጅና የሥራ አጋር አቶ ሞገስ ባልቻ በአዲስ አበባ ወዳጅነት አደባባይ የአስከሬን ሽኝት ሥነ-ሥርዓት ላይ እንደተናገሩት፤ ወንድሜ ግርማ የሺጥላን ከ2004 ጀምሮ በቅርበት አውቀዋለሁ። ወንድሜ ግርማ የሺጥላን ከማውቅበት ጊዜ ጀምሮ በባሕሪው ተጫዋችና መልካም አሳቢ ነበር። ነገር ግን መልካም ሃሳብ የነበረው ወንድማችንን ጽንፈኞች ነጥቀውናል ብለዋል።

የግርማን ሕያውነት የምናረጋግጠው ለሕዝብ የላቀ ጥቅም በመትጋት ነው ያሉት አቶ ሞገስ፤ አቶ ግርማ ሰውን ለመተዋወቅ ማንነትን፣ ድንበር እና አካባቢን አያይም። ይልቁንም ኢትዮጵያዊነትን የሚያስቀድም ታላቅ ፍቅር ያለው ወንድም ነው። በዓላማው ጽኑ፣ በአመነበት ጉዳይ ላይ አቋሙን የማይሸራርፍ፣ የሚመክር፣ ለሕዝብ እና ለሀገር የሚጠቅሙ ሃሳቦችን ወደፊት የሚያመጣም ነበር ብለዋል።

አቶ ግርማ ሰዋዊ ባሕሪው የሚያግባቡ ሃሳቦችን በማምጣት እና የጋራ ሚዛናዊ ጉዳዮችን በማንሳት የሚታወቅ ነው ያሉት አቶ ሞገስ፤ ወንድማችን ግርማ የሞተው በያዘው ሀሳብ እና ዓላማ ነው። ይህ ሐሳብ አይሞትም። ሀሳቡ የሚሞት ስላልሆነ፣ የግርማን ሕያውነት የምናረጋግጠው ለሕዝብ የላቀ ጥቅም በመትጋት ነው ብለዋል።

የኦሮሚያ ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ተሰማ በበኩላቸው፤ ጽንፈኝነት የሚያመጣውን መሪር መከራና ኃዘን ተረድተን አምርረን በመታገል ከኢትዮጵያ ምድር ከስር መሠረቱ እንዲነቀል ማድረግ አለብን። አለበለዚያ ወንድማችን ግርማን የሚመስሉ በንግግር መግባባት የሚችሉ ሌሎች ወንድሞቻችንን ልናጣ እንችላለን ብለዋል።

ግርማ ለቆመለት ዓላማ የኖረ በመጨረሻም አይተኬ ሕይወቱን ለሕዝብና ለሃገሩ የሰጠ ውድ የሕዝብ ልጅ ነው ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ ግርማ ሃገር፣ ሕዝብና መንግሥት የሰጠውን ታሪካዊ ኃላፊነት በፍጹም ቆራጥነት ተወጥቷል። እሱ ቢሞትም ሃሳቡና ዓላማው የሚሊዮን ጓደኞቹና የኢትዮጵያ ሃሳብ በመሆን ሳይንጠባጠብ ይሻገራል ብለዋል።

የሥራ ባልደረቦቹ የብልጽግና ፓርቲ አባላትና ሕዝቡም ጽንፈኝነት የሚያመጣውን መከራና መሪር ኃዘን ተረድተን አምርረን በመታገል ስር መሠረቱ ከኢትዮጵያ እንዲነቀል ማድረግ ይጠበቅብናልም ብለዋል።

በአማራ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የአስተዳደር ጉዳዮች ክላስተር አስተባባሪ ዶክተር ሰማ ጥሩነህ በበኩላቸው፣ አቶ ግርማ የሺጥላ፣ "መስዋዕት ሆነን ኢትዮጵያን እናፀናለን" የሚል አስተሳሰብ የነበረው ቀና ሰው ነበር ብለዋል።

በአማራ ክልል ውስጥ ያለውን ውስብስብ ሁኔታ ለመፍታት እና የኢትዮጵያ ብልጽግና እንዲረጋገጥ "የኅሐ ቃልኪዳን" የሚል አዲስ አስተሳሰብ እንዳፈለቁ የተናገሩት ዶክተር ሰማ፤ ልጆቹን፣ ዘመዶቹን ሳይል አጥፊዎቹንና ነፍሰ ገዳዮቹን ፊት ለፊት ተጋፍጦ እንደሚሞትም አምኖበት ወደ መስዋዕትነት የሄደ ጀግና የሕዝብ ልጅ ነው ብለዋል።

ሕዝብ ከሕዝብ የሚያበጣብጡ፣ ሰውን በመግደል የሚረኩ እና መግደልን መፍትሔ ያደረጉ አካላት ከትግላችን ወደ ኋላ አይመልሱንም ያሉት ዶክተር ሰማ፤ የወንድማችን የግርማን የብልጽግና ሕልም እና ሀሳብ ከግብ ለማድረስ ለሕዝባችን የበለጠ እንሠራለን። አቶ ግርማ ልጆቼን ቤተሰቤን ሳይል ለኢትዮጵያ የሠራ በመሆኑ ቤተሰቦቹን ከጎናቸው ሆነን፤ እንደ ግርማ ባንሆን እንኳ ድጋፋችንን ልናሳያቸው ይገባል ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

# 45 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎችን ከወባ በሽታ መታደግ ተችሏል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- እንደሀገር በተከናወኑ የመከላከል ሥራዎች ለወባ በሽታ ተጋላጭ የሆኑ 44 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሰዎችን ከወባ በሽታ መታደግ እንደተቻለ የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ ሰሞኑን እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ537 ወረዳዎች የሚውል 19 ነጥብ 7 ሚሊዮን አጎበር ተገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል። ከዚህ ውስጥ 16 ሚሊዮን 861 ሺህ በላይ አጎበር ለወረዳዎች ተሰራጭቷል።

ከዚህም ውስጥ 13 ሚሊዮን 859 ሺህ በላይ አጎበር ለተጠቃሚው ማኅበረሰብ የተሰራጨ ሲሆን 39 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሰዎችን ከወባ ትንኝ ንክሻ መታደግ መቻሉን ዶክተር ደረጀ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም 1 ሚሊዮን 207 ሺህ 897 ቤቶችን የፀረ-ወባ ኬሚካል በመርጨት 5 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕዝብ ከወባ በሽታ መከላከል እንደተቻለ ገልጸዋል።

በቀጣዩ የስርጭት ወቅት 1 ነጥብ 2 ሚሊየን ቤቶች ላይ የፀረ-ወባ ኬሚካል ርጭት ለማከናወን የሚያስፈልግ ግብዓት በግዥ ላይ እንደሚገኝ ዶክተር ደረጀ አስታውቀዋል።

የወባ በሽታ በኢትዮጵያ አንዱና ዋነኛው የኅብረተሰብ የጤና ችግር በመሆኑ በሽታውን መከላከል፣ መቆጣጠርና ማስወገድ ላይ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ድጋፍ የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

ከኢትዮጵያ የወባ በሽታን ለማስወገድ የባለ ድርሻ አካላትና የማኅበረሰብ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ዶክተር ደረጀ ተናግረዋል።

ማኅበረሰቡ በወባ መከላከል፣ መቆጣጠርና ማስወገድ ላይ አጎበርና ኬሚካል ከመጠቀም ባለፈ የአካባቢውን ጽዳት በመጠበቅ ረገድ ያለውን ግንዛቤ ለመጨመር የሚያስችሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እየተሠሩ መሆኑን አስረድተዋል።

የወባ ትንኝ ቁጥጥር ሥራዎችን ማጠናከር፣ የወባ በሽታ ምርመራና ሕክምና አገልግሎት መስጠት፣ የወባ በሽታ ቅኝትና ምላሽ ማጠናከር፤ የወባ በሽታን ከሀገራችን ለማጥፋት በመተግበር ላይ ያሉ ዋና ዋና ስልቶች መሆናቸውን ዶክተር ደረጀ አመላክተዋል።

አጎበሮችን በፍጥነት ለኅብረተሰቡ የማድረስ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ ነው። ማኅበረሰቡ በበኩሉ የአካባቢ ቁጥጥር ሥራዎችን በማከናወን በተለይ ግቢውንና አካባቢውን ለወባ ትንኝ መራቢያ ምቹ እንዳይሆኑ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በማፋሰስና በመደልደል በሽታውን ሊከላከል ይገባል ብለዋል።

በዝናብ ወቅት ውኃ ሊያቁሩ የሚችሉ ቦታዎችን ቀድሞ በማስተካከል የወባ አስተላላፊ ትንኝ እንዳትራባ ማድረግ ይገባል ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ በቀጣይ ከበልግ ዝናብ ጋር ተያያዞ የወባ ስርጭት መጠን እንዳይጨምር የጥንቃቄ ሥራዎች ማደግ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ከሚያዚያ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የዓለም ወባ ቀንን ምክንያት በማድረግ በወባ ላይ የተሠሩ የተለያዩ ጥናቶችንና የሳይንሳዊ ሲምፖዚያም በሐዋሳ ከተማ እንደሚካሄድም ዶክተር ደረጀ ገልጸዋል።

# ባለፉት ዘጠኝ ወራት ዘጠኝ ሚሊዮን የሚጠጉ ቱሪስቶች ክልሉን ጎብኝተዋል

## - 163 ሺህ ያህሉ የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች ናቸው

**በዳግማዊት ግርማ**



ፎቶ፡ በአጋጌ

አቶ ሁንዴ ከበደ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ዘጠኝ ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ክልሉን መጎብኘታቸውን ኦሮሚያ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ። 163 ሺህ ያህሉ የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች መሆናቸው ተጠቁሟል።

የክልሉ ባሕልና ቱሪዝም የቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሁንዴ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ኦሮሚያን ዘጠኝ ሚሊዮን የሚጠጋ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸውና ኢትዮጵያውያን ዜጎች ጎብኝተዋል። ክልሉን ከጎበኙት ዘጠኝ ሚሊዮን የሚጠጉ ቱሪስቶች ውስጥ ስምንት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ እንዲሁም 163 ሺህ ያህሉ የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች ናቸው።

አብዛኛውን የጎብኚ ቁጥር የሚይዙት በክልሉ በበርካታ ስፍራዎች ላይ የተከናወነው የኢሬቻ ፌስቲቫልና በክልሉ የሚደረጉ መንፈሳዊና ሕዝባዊ በዓላት መሆናቸውን የገለጹት አቶ ሁንዴ፤ የአዲስ አበባውን ጨምሮ 63 መዳረሻዎች ላይ የተከበረው ኢሬቻ፣ ቁልቢ ገብርኤል፣ ደብረሊባኖስ ንግስ በዓላት ላይ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ጎብኚዎች መሳተፋቸውንም ገልጸዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ክልሉን ከጎበኙት የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ስምንት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር መገኘቱን የቢሮው ምክትል ኃላፊ ተናግረዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት ለቱሪዘም ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራቱን ያመላከቱት አቶ ሁንዴ፤ በዚያው ልክ ደግሞ ዓለም ላይ ይከሰታል ተብሎ ያልታሰበው የኮቪድ 19 እንዲሁም በሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው የሰላም እጦት ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ የነበረው የውጭ ሀገራት ቱሪስት ፍሰት አነስተኛ መሆኑን አውስተዋል።

በፌደራል መንግሥትና ሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለይም ካለፉት ሦስትና አራት ወራት ወዲህ የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከፍተኛ የሆነ መነቃቃት መታየቱንም ገልጸዋል። አቶ ሁንዴ የኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ በክልሉ የሚደረጉ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች ከዚህም በላይ ለማሳደግ የተለያዩ አሠራሮችን በመዘርጋት በመሥራት ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

ዜና

# “ጽንፈኝነት የአማራ ክልል ሕዝብ ላይ የተቃጣ አደገኛ የመከራ በትር ነው”

\- ዶክተር ይልቃል ከፋለ
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ጽንፈኝነት መጠፋፋት ላይ ተመሥርቶ ሕዝብ ላይ የተቃጣ አደገኛ የመከራ በትር እንጂ ለድል የሚያበቃ የትግል ስልት አይደለም ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ተናገሩ።

የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባል የነበሩት አቶ ግርማ የሺጥላ ልዩ ቦታው መንዝ ጓሳ በተባለ አካባቢ እሳቸውን ጨምሮ በሹፌራቸውና በጠባቂዎቻቸው ላይ በተፈጸመ ጥቃት ሕይወታቸው አልፏል።

በአዲስ አበባ ወዳጅነት አደባባይ በተካሄደው የአቶ ግርማ የሺጥላ የአስከሬን ሽኝት ሥነ-ሥርዓት ላይ ዶክተር ይልቃል ከፋለ እንደተናገሩት፤ በተከታታይ በአመራሮች ላይ የሚደረገው ግድያ የአማራን ሕዝብ ስቃይ እና መከራ ለማራዘም የሚሠሩ ጽንፈኛ ኃይሎች ማሳያ ነው። ጽንፈኝነት መጠፋፋት ላይ ተመሥርቶ ሕዝብ ላይ የተቃጣ አደገኛ የመከራ በትር እንጂ ለድል የሚያበቃ የትግል ስልት አይደለም።

ጽንፈኛ ኃይሎች ወንድማችን ግርማ የሺጥላን ነጥቀውናል ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ይህ ጽንፈኝነት በዘመናት የተገነባውን ልማት የሚያወድም እንጂ ለሕዝባችን ተስፋ የሚፈነጥቅ አይደለም። ስለሆነም መላው ሕዝባችን ይህን አስነዋሪ፣ አሳፋሪና አዋራጅ ድርጊት በማውገዝ አጥፊዎችን በሕግ አደባባይ ለማቅረብ በሚደረገው እንቅስቃሴ የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይገባል ብለዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ክልሉ በጦርነት ውስጥ ያለፈ መሆኑን የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በተከታታይ ሕዝቡ ላይ የደረሰው ኀዘን ሳይረግብ የአማራ መሪዎችን በማጥፋት ችግሩ ሁሉ ይፈታል በሚል ራስን በራሱ በሚያጠፋ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ የተደራጁ ኃይሎች ተከታታይ ጥፋት እያደረሱ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ይህ ጽንፈኝነት ሕዝቡን በመከፋፈል ጊዜ ያለፈበትን እርስ በርስ መገዳደል በማምጣት በሕዝባችን ላይ ተስፋ መቁረጥን እና የተሸናፊነት ሥነ-ልቦናን በመገንባት የሚጠናቀቅ እንጂ ለድል የሚያበቃ አይደለም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የወንድማችን የግርማ የሺጥላ መሥዋዕትነት ለመላው አመራራችን የሚያስተላልፈው መልዕክት በትግል የመጽናናት አስፈላጊነትን እና የጀመርነውን የማልማት እንዲሁም ሰላም የማረጋጋት ትግልን በፅናት የማስቀጠል አደራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህ ኀዘን ውስጥ ሆነን ትግላችን ፍሬ አፍርቶ ወንድማችን ግርማ የሺጥላ ሲታገል እና ሲያታግል የነበረውን ሐሳብ እና አጀንዳ በመያዝ፣ ቃልኪዳናችንን የበለጠ በማደስ ለበለጠ ትግል እና ድል እንድንነሣ ጥሪዬን ለአመራራችን አቀርባለሁ ብለዋል።

ዶክተር ይልቃል፤ ታጋዩ፣ ታታሪውና ቆራጡ አቶ ግርማ የሺጥላ አድፍጠው መንገድ ላይ በጠበቁት ጽንፈኞች በመቀጠፉ በእጅጉ ማዘናቸውን ገልጸው፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለሥራ አጋሮቻቸው እንዲሁም ለቤተሰባቸው መጽናናትን ተመኝተዋል።

# “የወንድማችንን ገዳዮች መንግሥትና ሕዝብ በመረባረብ ለፍርድ እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለን”

• አቶ ኃይሌ የሺጥላ
የአቶ ግርማ የሺጥላ ወንድም

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአቶ ግርማ የሺጥላ ገዳዮችን መንግሥትና ሕዝብ በመረባረብ ለፍርድ እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለን ሲል ወንድማቸው አቶ ኃይሌ የሺጥላ ተናገረ። ወንድማቸው ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ አቅመ ደካማ እናቱንና ሕጻናት ልጆቹን በትኖ ያለፈ በመሆኑ የመንግሥትና የሕዝብ ድጋፍ እንዳይለየን ሲልም ጥሪ አቅርቧል።

የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የነበሩት የአቶ ግርማ የሺጥላ የአስከሬን ሽኝት በትላንትናው እለት በወዳጅነት አደባባይ ላይ በተካሄደበት ወቅት ንግግር ያደረገው ወንድማቸው አቶ ኃይሌ የሺጥላ እንደተናገረው፤ ወንድማቸው ከልጅነቱ ጀምሮ ተጫዋች፣ ተግባቢ፣ ቅን፣ በቤተሰባቸውና በቤተ ዘመዱ ተወዳጅ፤ ሰው አክባሪና ሩህሩህ እንደነበር ገልጿል። በቤተሰቡ ውስጥ በተለይም አባታችን ከተለየን ወዲህ ቤተሰቡን የመምራትና የማስተዳደር ድርብ ኃላፊነት የተሸከመ አለኝታችንና ጋሻችን ነበረም ብሏል።

ወንድማቸው ግርማ ቤተሰቡን ከማስተዳደርና ከመምራት ጎን ለጎን በተለያዩ ተቋማት መንግሥትና ሕዝብን ማገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሌትተቀን ሲተጋና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ይሠራ የነበረ የሕዝብ ልጅ መሆኑን ሀገር የሚያውቀው ሐቅ እንደነበርም ተናግሯል። ለራሱና ለቤተሰቡ ሳይኖር፣ ሳያዳላ ራሱን ለሀገርና ለሕዝብ አሳልፎ የሰጠ እውነተኛ የሕዝብ ልጅ ነበር ሲልም ገልጿል።

ከሁሉም በላይ ለሀገርና ለሕዝብ ቅድሚያ በመስጠት በመንግሥት ሥራ ላይ እያለ ባላሰብነው እና ባልጠበቅነው ሁኔታ ሩቅ አሳቢ የነበረው ወንድማችንን በአጭሩ ቀጭተውብናልም ብሏል። በዚህም ምክንያት ወደር የለሽና መሪር የሆነ ሀዘን ደርሶብናልም ነው ያለው ወንድማቸው።

ከጥቃቱ በኋላ ሕይወታቸውን ማትረፍ ባይቻልም ችግሩ መፈጠሩ ከታወቀበት ቅጽበት ጀምሮ በመንግሥትና ሕዝብ በኩል ለተደረገው ርብርብ ምሥጋና እናቀርባለን ያለው አቶ ኃይሌ፤ ከዚህም ባሻገር ለተደረገው ደማቅ የክብር አሸኛኘት ፕሮግራም በራሱና በመላው ቤተሰቡ ስም ምስጋና አቅርቧል።

የወንድማችንን ገዳዮች መንግሥትና ሕዝብ በመረባረብ ለፍርድ እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለንም ብሏል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ ለተገኙ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ወዳጅ ዘመዶቻቸውም በቤተሰቡ ስም ምስጋና አቅርቧል።

በአቶ ግርማ የሺጥላ ላይ የተፈፀመው ግድያ ባሳለፍነው ሐሙስ እለት ከሰዓት በኋላ፤ የመንግሥትና የድርጅት ሥራዎችን ሠርተው ከመሐል ሜዳ ወደ ደብረ ብርሃን ሲመለሱ በመንዝ ጓሳ ላይ እንደሆነ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መግለጹ የሚታወስ ነው።

# የብልጽግና ጉዞ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ አደም፤ መላው የፓርቲው አመራሮችና አባላት እሱ የተሰዋለትን ዓላማ ከዳር ለማድረስ እንተጋለን ብለዋል።

ወንድም ግርማ እጅግ ሰው ወዳድ ቅንና ተግባቢ፤ ሰብዓዊነትን የተላበሰ ሰው ነበር ያሉት አቶ አደም፣ ሀገራዊ ራዕይን የሰነቀ በሳልና ቁርጠኛ የሕዝብ አገልጋይ መሪ እንደነበረም አንስተዋል። የኢትዮጵያን እውነታና የአማራ ሕዝብ ዘላቂ መብትና ጥቅም የሚከበርበትን አግባብ በሚገባ የተረዳ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ለጋራ ብልጽግና ሊያደርስ የሚችል ዲሞክራሲያዊና ሕዝባዊ አስተሳሰብን የተላበሰና ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር አስፈላጊ የሆነውን የትስስር ድልድይ ሌት ተቀን ሲገነባ የነበረ አርቆ አሳቢ መሪ እንደነበረም አንስተዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ልዩነት ሰባኪነትን የሚጸየፍ፣ ጽንፈኝነትን አምርሮ የሚታገልና ሁሌም ለፍትሕና ለእኩልነት የቆመ እውነተኛ የብልጽግና አመራር ነበር ያሉት አቶ አደም ፋራህ፤ ለሀገርና ለሕዝብ ይጠቀማል ብሎ የሚያስበውን በግልፅ የሚያቀርብና በምክንያታዊነት የሚሞግት ጀግና ልባም መሪ እንደነበረም ተናግረዋል።

አቶ አደም እንደገለጹት፤ ተግባሩን የፈጸሙት ከሰውነት ተራ የወጡ ወደ አውሬነት የተቀየሩ ጽንፈኞች ናቸው፤ የሕዝብን መሪ እየገደሉ የንጹሓን ዜጎችን በሕይወት የመኖርና የአካል ደህንነት መብትን እየገፈፉ ሊሳካ የሚችል ዘላቂ ጥቅም የለም፤ እነኝህ ጽንፈኞች ወንድማችንን የገደሉት በሀሳብ ልዕልና በመርሕ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ትግል እንዳይኖር ለማድረግና ለሥርዓት አልበኝነት የተመቸ ሁኔታ በመፍጠር የግልና የቡድን አላማቸውን ለማሳካት ነው፤ ይህ ግን በፍጹም የሚሳካ አይሆንም።

“በኢትዮጵያ ውስጥ ሥርዓት አልበኝነት፣ ንጹሐንን መግደል፣ የሕዝብን መሪ መግደል የከፋ ዋጋ እንደሚያስከፍል እናረጋግጣለን” ብለዋል።

ገዳዮችን ለሕግ ለማቅረብ አበክረን እንሠራለን ያሉት አቶ አደም የሕዝቡን ታሪክና ባህል ለማጉደፍ የሚታትሩ ጽንፈኞችን ሥርዓት ለማስያዝ በሚደረገው ጥረት ኅብረተሰቡ ከመንግሥት ጎን በመቆም አጥፊዎችን ለሕግ የማቅረቡን ሥራ እንዲያግዝ ጥሪ አቅርበዋል። ብልጽግና ፓርቲ ከአቶ ግርማ የሺጥላ ቤተሰቦች ጎን እንደሚቆምም አረጋግጠዋል።

በሽኝት መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ኃዘናቸውን የገለፁት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ የአቶ ግርማን ሞት መስማት አብረነው ለሠራነው አመራሮች አስደንጋጭ ነው፤ እውነት ፈጦ መጥቷልና ይህንን እውነት ተቀብለን አቶ ግርማ የኖረለትንና የተሰዋለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ልንበረታ ይገባል ብለዋል።

የለውጡ ጎዳና ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ያጋጠሙንን ፈተናዎች ሁሉ በጽናት በመታገል እራሱን ሰጥቶ የታገለ ጀግና መሪ እንደነበር ያስታወሱት ከንቲባዋ፤ ግርማ እድለኛ ነው፤ ላመነበት ዓላማ በጀግንነት መሰዋት ችሏል ብለዋል።

ሥጋን መግደል ቢቻልም እውነትን መግደል አይቻልም ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ ግርማ በእውነት የኖረላቸውን የሕዝቦች አንድነት፣ የኢትዮጵያ ብልጽግና እና ወንድማማችነትን አፅንተን እንቀጥላለን ነው ያሉት።

አቶ ግርማ የሺጥላ ሕዝብን ለማገልገል ድንበር የማያውቅ እና ቅን ሰው እንደነበር ያስታወሱት ከንቲባዋ፤ ግርማ የሞተለት ዓላማ ሊገደል የሚችል አይደለም፤ ግርማ የማይሞት ዓላማ ያነገበ መሪ በመሆኑ ላመነበት እውነት ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠትም ደርሷል ብለዋል።

አቶ ግርማ አብሮ መሥራት የሚወድ ፣መተባበር የሚያውቅ፣ ሕዝብን ለማገልገል የቆረጠ መሪ እንደነበርም ከንቲባ አዳነች ተናግረዋል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የፌደራል እና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸው፣ የትግል አጋሮቻቸው እና ቤተሰቦቻቸው ተገኝተዋል።

በሥነሥርዓቱ ላይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤና የአቶ ግርማ ቤተሰብ ተወካይ አቶ ኃይሌ የሺጥላ የአበባ ጉንጉን አኑረዋል።

# የአቶ ግርማ የሺጥላ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አመራር መሆኑን ያልተረዱ ልጆችንን ነጥቀውናል ብለዋል።

ሥርዓተ ቀብሩ ላይ ተናድደን እና አልቅሰን መለያየት ሳይሆን ግርማ ለተሰዋለት ዓላማ እስከመጨረሻው ድረስ ውስጣዊ አንድነትን አጠናክረን ዳር ማድረስ አለብን ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ የአቶ ግርማ ሀሳብ የሚሞት ሳይሆን ክልልና ሀገርን የሚቀይር አንድነትን የሚያመጣ እንደሆነም ገልጸዋል።

በውይይት የማይፈታ ነገር የለም ያሉት ዋና አስተዳዳሪው ሁሉንም በሰከነ መንገድ ማየትና መፍታት ይገባል፤ ቤተሰቦቹም እንዳይቸገሩ መደገፍና መንከባከብ ይገባናል ብለዋል። የሰሜን ሸዋ ዞን ከአቶ ግርማ ጋር የተሰዉ የጸጥታ አካላትን ቤተሰቦችም እንደሚያስብና እንደሚንከባከብ እንዲሁም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

የአቶ ግርማ የሺጥላ ወንድም አቶ ኃይሌ የሺጥላ በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደተናገረው፤ ወንድሜ ተጫዋች፣ ተግባቢ፣ ቅን፣ በቤተሰባቸውና በቤተ ዘመዱ ተወዳጅ፤ ሰው አክባሪና ሩህሩህ ነበር። አባታችን ከተለየን ወዲህ ቤተሰቡን የመምራትና የማስተዳደር ድርብ ኃላፊነት የተሸከመ የቤተሰቡ አለኝታና ጋሻ ነበር ብሏል።

ወንድሜ ቤተሰቡን ከማስተዳደር ጎን ለጎን በተለያዩ ተቋማት መንግሥትና ሕዝብን ማገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የሚሠራ ነበር ያለው አቶ ኃይሌ፤ ራሱን ከቤተሰቡ በላይ ለሕዝብ አሳልፎ የሰጠ እውነተኛ የሕዝብ ልጅ ነበር ብሏል።

ለሀገርና ለሕዝብ ቅድሚያ በመስጠት በመንግሥት ሥራ ላይ እያለ ባላሰብነው እና ባልጠበቅነው ሁኔታ ሩቅ አሳቢ የነበረውን ወንድማችንን በአጭሩ ቀጭተውብናል ያለው አቶ ኃይሌ፤ የወንድማችንን ገዳዮች መንግሥትና ሕዝብ በመረባረብ ለፍርድ እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለን ብሏል። ከጥቃቱ በኋላ ሕይወታቸውን ማትረፍ ባይቻልም አስከሬኑ በክብር እንዲሸኝ ስላደረጋችሁም እናመሰግናለን ሲል ተናግሯል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጽንፈኝነትና ጥላቻ የሁልጊዜም የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው!

ጥላቻ የሚጠላውን ብቻ ሳይሆን ጠይውንም ራሱን ቀስ በቀስ የሚበላ ክፋት ነው። በጥላቻ ላይ የተገነባ የትኛውም ዓይነት አስተሳሰብ ፍጻሜው ጥፋትና ኪሳራ ብቻ ነው። ለዚህም በጥላቻ ተጀምረው በከፍተኛ ውድቀት የተፈጸሙ ታሪኮችን ዓለማችን በየዘመኑ አስተናግዳለች፤ ዛሬም ቢሆን ከዚህ የአስተሳሰብ እርግማን መሻገር የሚያስችላትን የተሟላ አቅም ማግኘት ባለመቻሏ ተጨማሪ ዋጋ ለመክፈል ተገዳለች።

በተለይም ጥላቻን እንደ አንድ የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙ ግለሰቦችና ቡድኖች፤ በተደራጀና በተጠና መንገድ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚዘሯቸው የጥላቻ ዘሮች ወቅቱን ጠብቀው የሚያፈሯቸው ፍሬዎች የሚኖሩባቸውን ማኅበረሰቦች እያስከፈሉ ያለው ዋጋ ከግምት በላይ እየሆነ ነው። ዓለምንም በብዙ መልኩ መረጋጋት እያሳጣት ይገኛል።

እንዲህ ዓይነቱ የአስተሳሰብ ርግማን የሩዋንዳ፣ የብሩንዲ ፣ የሶማሊያ ፣ የሱዳን ... ወዘተ ሕዝቦችን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈላቸው፣ እነዚህን አገራት አለመረጋጋት አሳጥቶ ሕዝቦቻቸው የተሻሉ ነገዎችን ተስፋ አድርገው እንዳይንቀሳቀሱ ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነባቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። ከጠባቂነት ወጥተው ራሳቸውን አሸንፈው ቀና ብለው መጓዝ እንዳይችሉም አድርጓቸዋል።

ዘመኑ የደረሰበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እድገት በራሱ፤ ይህ የጥፋት አስተሳሰብ በቀላሉ ወደ የማኅበረሰቡ እንዲሰራጭ አስቻይ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። በዚህም ችግሩን ለመቆጣጠር የሚደረጉ አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጥረቶችን የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ እንዳይሆን፤ ብዙዎች ዛሬ ላይም በየዋህነት የአስተሳሰቡ ሰለባ እንዲሆኑም አድርጓል።

በእኛም አገር ቢሆን አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ጥላቻን መሠረት ባደረገ ትርክት የፖለቲካውን መድረኩን የመደባለቃቸው እውነታ፤ አገር እንደአገር የዚህ የአስተሳሰብ ሰለባ እንድትሆን እያደረጋት ይገኛል። ላለፉት አስርት ዓመታት ጥላቻን መሠረት አድርገው የተዘሩ ትርክቶች በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት ከፉ ፍሬ አፍርተው ዜጎችን ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል።

ሕዝቦቿ በመቻቻልና በመከባበር በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወቁባት አገራችን ፤ የጥላቻ ትርክቶች በፈጠሯቸው ውዥንብሮች ብዙ ሺዎች ለሞት፤ ሚሊዮኖች ለስደት ተዳርገዋል። ጥቂት የማይባሉ የትውልዱ ተስፋዎች በዚህ የአስተሳሰብ ህመም ተይዘው፤ ለራሳቸውና ለአገራቸው ነገዎች ተስፋ ከመሆን ይልቅ ስጋት ሆነዋል።

እውነታው ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ እንደአገር አገር ይዛ በተነሳችው የበለጸገች የጋራ አገር ምስረታ ራዕይ ላይ የፈጠረው አሉታዊ ተጽእኖ ለውጡን ወደኋላ ከመጎተት አልፎ፤ ዜጎች በለውጡ ላይ የነበራቸውን ተስፋ በማጨለም ትናንቶችን ናፋቂ እንዲሆኑ አስገድዷቸዋል። ይህንን ለመቀልበስ የለውጡ ኃይል ለመሄድ የተገደደበት ርቀትና ያስከፈለው ዋጋ ቀለል ተደርጎ የሚታይ አይደለም።

አሁን ላይ እነዚህ የጥላቻ ትርክቶች እንደ አገር የፈጠሩብንን ተግዳሮቶች ለዘለቄታው ችግር በማይሆኑበት ደረጃ አክመን መሻገር የሚያስችለንን የአስተሳሰብ አቅም መገንባት ካልቻልን፤ ችግሩ ካለው ከፉ ባህሪ አንጻር መጪውንም ትውልድ ያልተገባ ተጨማሪ ዋጋ ማስከፈሉ የማይቀር ነው። ለዚህም ደግሞ እንደ ትውልድ የተጠያቂነት ደረጃው ከፍያለ ነው።

ጥላቻ ማኅበረሰብ ከተገነባበበት መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች አንጻር የማንነት ግራ መጋባት ከመፍጠር፣ በብዙ የጥፋተኝነት መንፈስ እራስን እንዲኮንን ከማድረግ እና ሰላሙን ከመናጠቅ የዘለለ የሚያተርፍለት ነገር አይኖርም፤ እስከዛሬ ባለውም ያተረፈለት ነገር የለም።

የጥላቻ ሳባኪዎችም ቢሆን ከስብከታቸው የተነሳ በሚፈጠር ጥፋት ከመፈንጠዝ ፤ በዚህም ሕዝባችንን ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ ጥፋትና ጽንፈኝነት ወደመሻታቸው መቼም ቢሆን ሊያደርሳቸው አይችልም። የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የተሸከሙት የጥላቻ ካንሰር እነሱን በልቶ መጨረሱ የማይቀር ነው።

መላው ሕዝባችን ይህንን እውነታ ዘመናትን ካሻገሩት መንፈሳዊ ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶች አንጻር በሰከነ መንፈስ በመመርመር፤ አሁን የተጀመረውና ፍሬው እየታየ ያለው የሰላም መንገድ የበለጠ ፍሬ እንዲያፈራ በቁርጠኝነትና በኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። የመጪውን ትውልድ ዕጣ ፈንታ የሚወስነው ዛሬ ላይ እንደአገር እየጣልነው ያለው የሰላም መሠረት እንደሆነም ሊያስተውለው ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## የአቶ ግርማ የሺጥላ አጭር የሕይወት ታሪክ



አቶ ግርማ የሺጥላ ወ/ጻዲቅ ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘውዴ ስመኝ ከአባታቸው ከአቶ የሺጥላ ወልደጻዲቅ በቀድሞው ሸዋ ክፍለ ሃገር በመንዝና ግሼ አውራጃ በጌራ ምድር ወረዳ መሐል ሜዳ ከተማ ኅዳር 17 ቀን 1967 ዓ.ም ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የአንደኛና መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመሐል ሜዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቅ ችለዋል።

ገና በአፍላ ወጣትነት ዕድሜያቸው ከሰኔ 1986 ዓ.ም ጀምሮ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በአንጾኪያ ወረዳ የተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤት የስራ ባልደረባ በመሆን የመንግሥትን ሥራ አሀዱ ብለው ጀምረዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ በወጣትነታቸው ባሳዩት ትጋትና ታታሪነት ምክንያት ለኃላፊነት የታጩ ሲሆን ከ1989 ዓ.ም እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት በሰሜን ሸዋ ዞን የአንጾኪያ ወረዳ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ሕዝባቸውና መንግሥት የጣለባቸውን ኃላፊነት ተወጥተዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ለትምህርት በነበራቸው ልዩ ጉጉትና ፍላጎት ምክንያት የትምህርት ዕድል እንዲመቻችላቸው ዘወትር ጥያቄ ያቀርቡ ስለነበረ የተሰጣቸውን የመንግሥትና የሕዝብ ኃላፊነት ከማከናወን ጎን ለጎን ከግል ኮሌጅ በማኔጅመንት በዲፕሎማ ተመርቀዋል።

የተከበሩ አቶ ግርማ የሺጥላ በነበራቸው የሥራ ታታሪነትና አስተዋይነት እንዲሁም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በሚያገለግሉት ማኅበረሰብ ከፍ ያለ ተቀባይነት ስለነበራቸው ከ1990 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 1995 ዓ.ም ድረስ የአንጾኪያ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ በመሆንም አገልግለዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ በታችኛው እርከን በነበራቸው የአመራር ብቃትና ልዩ ተሰጥዖና ልምድ ምክንያት ለዞን ከፍተኛ ኃላፊነት ተመርጠው ወደ ሰሜን ሸዋ ዞን በመዛወር ከፍ ያሉ ኃላፊነቶችን ሲወጡ ኖረዋል።

ከጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም ጀምሮ የሰሜን ሸዋ ዞን ብአዴን ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን ቀጥለውም ከመስከረም 1997 ዓ.ም እስከ ኅዳር 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በሰሜን ሸዋ ዞን የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን የከተማውን ሕዝብ አገልግለዋል።

በኋላም ከታኅሳስ 01 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ በሰሜን ሸዋ ዞን የባሶና ወራና ወረዳ ማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃለፊ በመሆን በየደረጃው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት፣ በብስለት እና በትጋት ከተወጡ በኋላ እንደገና ተመልሰው ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ መስከረም 2000 ዓ.ም ድረስ የሰሜን ሸዋ ዞን የሕዝብ ግንኙነት አማካሪ በመሆን አገልግለዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ በደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ካገኙ በኋላ ወደ ሥራ በመመለስ የሰሜን ሸዋ ዞን ብአዴን አደረጃጀት እንዲሁም እስከ መስከረም 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ የሰሜን ሸዋ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ በመሆን የተሰጣቸውን የሥራ ኀኃላፊነት በብቃት ተወጥተዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ከጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የሰሜን ሸዋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ በመሆን ካገለገሉ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ወደአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመሄድ ትምህርታቸውን ጀምረዋል። በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ማለትም በኮተቤ ሜትሮ ፖሊቲያን ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሲማሩ ቆይተው በኢኮኖሚክስ ተመርቀዋል።

የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቻውን እንዳጠናቀቁ ከመስከረም 2013 ዓ.ም ጀምሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ በመሆን የክልሉን ሕዝብና መንግሥት በትጋት አገልግለዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ከመስከረም 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ሕይወታቸውን በድንገተኛ አደጋ እስከተነጠቁበት ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ የብልጽግና ማዕከላዊ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚና የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ በስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ በባሶና ወራና ወረዳ የቀይት ምርጫ ጣቢያ የክልል ምክር ቤት ዕጩ በመሆን ተወዳድረው ሕዝቡ የሰጣቸውን ውክልና በኃላፊነት ስሜት ሲወጡ ቆይተዋል።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትንና የክልሉን ሕዝብ ወክለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደሬሽን ምክር ቤት አባል በመሆን የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሲወጡ የቆዩ ወሳኝ አመራር ነበሩ።

አቶ ግርማ የሺጥላ ከመደበኛ ሥራ በተጓዳኝ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ቦርድ አባል ሆነው ያገለገሉ ሲሆን የደብረ ብርሃን ሪፈራል ሆስፒታል ሥራ አመራር ቦርድን እና የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ሥራ አመራር ቦርድን በሰብሳቢነት መርተዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ከልጅነት እስከ እውቀት በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች ተመድበው ሲሠሩ መቆየታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. ወዲህ በተደጋጋሚ የተከፈተብንን ጦርነት ለመቀልበስ ጉልህ ድርሻ ነበራቸው።

በተለይም በሁለተኛውና በሦስተኛው ጦርነት ወቅት የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር ግንባር ቀደም መሪ በመሆን እስከ ውጊያ ወረዳ ድረስ በመግባት የክልሉ ሕዝብ የተቃጣበትን የሕልውና አደጋ ለመቀልበስ ራሳቸውን ለመስዋዕትነት አዘጋጅተው ከፍተኛ አሰተዋፅዖ ያበረከቱ ቅንና አስተዋይ መሪ ነበሩ።

አቶ ግርማ የሺጥላ ከ25 ዓመታት በላይ የክልሉን መንግሥትና ሕዝብ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ያለመታከት ማገልገላቸው የሚዘነጋ አይደለም። ከወጣትነት እድሜያቸው ጀምሮ ሕይወታቸውን በግፍ እስከተነጠቁበት ቀን ድረስ ራሳቸውን ለክልሉ ሕዝብ ጥቅም በግንባር ቀደምነት አሰልፈው ደፋር አመራር አረጋግጠዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ብርቱ፣ ታታሪና ለቆሙለት ዓላማ ግንባራቸውን የማያጥፉ፣ የተሰጣቸውን ኃላፊነት የሚያከብሩ፣ ለአማራ ሕዝብም ሆነ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይታክቱ የደከሙና ብልህና አዋቂ የሕዝብ መሪ እንደሆኑ አብረዋቸው የሠሩ የሥራ ባልደረቦቻቸው ሁሉ የሚመሰክሩላቸው ሐቅ ነው።

አቶ ግርማ የሺጥላ ለሥራ በወጡበት ወቅት የክልሉን ሕዝብ ጥቅም ዛሬም ሆነ ዘወትር የማምከን ሕልምና ትልም አንግበው ከሚንቀሳቀሱ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ድንገት በተተኮሰባቸው ጥይት ሚያዚያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በተወለዱ በ48 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ባለትዳር ሲሆኑ የሶስት ሴት እና የአራት ወንድ ልጆች አባት ነበሩ።

አቶ ግርማ የሺጥላ በደረሰባቸው አስደንጋጭና ድንገተኛ ህልፈተ ሕይወት ለመላው ቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው፣ ለሥራ ባልደረቦቻቸው፣ ለትግል አጋሮቻቸው እና ለመላው የአማራ ክልል ሕዝብ መፅናናትን እንመኛለን።

ፈጣሪ ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት ያኑርልን ።

# ፋሽን

## የፋሽን ተደራሽነት እየተስፋፋ መምጣት

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የፋሽን ዲዛይነሯ ሰርካለም ኮራ

ቀደም ሲል በአገራችን ለፋሽን ኢንዱስትሪው የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ ሆኖ ቆይቷል:: አሁን ላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለፋሽን የሚሰጠው አመለካከት እየተለወጠ መጥቷል፤ በዚያው ልክ ተደራሽነቱም እየሰፋ መነቃቃት እያሳየ መምጣቱን በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይገልጻሉ::

የፋሽን ተደራሽነትን የማስፋት ሥራ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማስተዋወቅን ይጠይቃል:: አሁን ፋሽንን በመድረክ ትርዒት ከማስተዋወቅ ባሻገር የተለያዩ አማራጮች በመጠቀም የማስተዋወቅ ሥራዎች ሲሠሩ እንመለከታለን:: ባለሙያዎቹ የፋሽን ተደራሽነትን ለማስፋት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እየጨመሩ መምጣታቸውንና ወቅቱ ለፋሽን መልካም የሚባል እንደሆነም ይገልጻሉ::

የፋሽን ዲዛይነሯ ሰርካለም ኮራ እንደምትለው፤ ፋሽን በአይን የሚታይ ጥበብ (አርት) ነው:: ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ የራሱን ሀሳብ፣ አመለካከትና ውበት የሚገልጽበት መንገድ ነው:: ለሚያየው ሰው ደግሞ የእይታ ጉዳይ መሆኑን ትገልጻለች::

ያለንበት ዘመን የግሎባላይዜሽን እንደመሆኑ መጠን ፋሽንን ለማስተዋወቅ አሁን ያለው ሁኔታ ቀደም ሲል ከነበረው ይሻላል የምትለው ዲዛይነር ሰርካለም፤ እንደፌስ ቡክ፣ ኢንስታግራም፣ ቲክቶክ ዓይነት የማህበራዊ ሚዲያዎችንና የኔትወርክ አማራጮች በመጠቀም የፋሽን ተደራሽነትን ማስፋት እንደሚቻል ትጠቁማለች:: የተለያዩ ፋሽን ትርዒት መድረኮች በመጠቀም እይታ ማግኘት ለፋሽን ተደራሽነቱ አስተዋፅኦ እንዳለው ትናገራለች::

በሌላ በኩል ታዋቂና ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች በመጠቀም በማስተዋወቅ ይቻላል:: በተለይ ወጣቶች ታዋቂና ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች የሚለብሱትን ፋሽን ስለሚከተሉ ያንን አማራጭ መጠቀም የፋሽን ተደራሽነት የሚሰፋበትን መንገድ ማስፋት የሚቻል መሆኑን ነው የምትገልጸው::

የፋሽን ኢንዱስትሪውን ለማስተዋወቅ በብሪትሽ ካውንስል፣ በኢንኩቤሽን ማዕከላት፣ በአፍሪካ ዊክ ፋሽንና በግለሰቦችም እየተደገፉ የሚዘጋጁ መድረኮችም መኖራቸውን የምትገልጸው ዲዛይነሯ፤ እሷ ከእነዚህ መድረኮች በተጨማሪ ቲክቶክ፣ ኢንስታግራም፣ ፌስ ቡክ፣ የመሳሰሉትን የማህበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞችን በመጠቀም የፋሽን ሥራዎቿን ተደራሽ ለማድረግ እየሞከረች ነው::

‹‹ቀደም ሲል ለፋሽን ኢንዱስትሪ ትኩረት አይሰጠውም ነበር›› የምትለው ዲዛይነሯ፤ አሁን ላይ ትምህርቱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃም እየተሰጠ መሆኑንና በዘርፉ በጣም ብዙ ዲዛይነሮች ስላሉ የፋሽን ተደራሽነት ከምንም ጊዜውም በላይ እየሰፋ ነው ትላለች:: በተለይ ወጣቶች ትኩረት ሰጥተው እየሠሩበት እንደሆነም ነው የምትጠቅሰው::

በመንግሥት በኩል ፋሽን ላይ ለተሰማሩ ሰዎች የመስሪያ ቦታዎች በመስጠት እና ማሽነሪዎች ለመግዛት 15 በመቶ ቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ በረጅም ጊዜ ክፍያ እንዲሰጥ በማድረግ የሚደረጉ ድጋፎች ዘርፉ እንዲስፋፋ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብላለች::

በሌላ በኩል የፋሽን ኢንዱስትሪው እንዳይስፋፋ የሚያደርጉ ብዙ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ጠቅሳ፤ በተለይ ጨርቃጨርቅ ላይ የሚታዩ ችግሮች ከሥራው አንጻር የታሰበው ዓይነት ሥራ ለመሥራት እንደማያስችሉና አንዳንዴም ለኪሳራ የሚዳርጉ መሆናቸውን ነው የምትጠቁመው:: ‹‹እኔ መሥራት የምወደው በሁነት (በኢቨንት) ጊዜ የሚለበሱ ልብሶችን ነበር›› የምትለው ዲዛይነሯ፤ ሆኖም ግን የውስጤን እንዳልኖር ያደረገኝ የምፈልገውን ጨርቅ በፈለግኩት መልኩ ለመጠቀም ከፋብሪካ ጀምሮ የአቅርቦትና ሌሎች ተደራራቢ ችግር ያሉበት መሆኑን ትገልጻለች ::

ፋሽን እንዲበረታታ የሚያደርጉ መድረኮች በማዘጋጀት ረገድ ኢንቨስተሮች ስፖንሰር ከማድረግ ጀምሮ መድረኮች በማዘጋጀትና በመደገፍ የፋሽን ዘርፉን ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው የጠቆመችው ዲዛይነሯ፤ ፋሽን ፈጠራዊ የሆነ እይታ የሚፈልግ ስለሆነ ማበረታታትንና ሞራል የሚሰጥን እንደሚፈልግ ጠቁማለች::

ፋሽን ኢንዱስትሪው እንዲያድግ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋንኛው ወደ ውስጥ ማየት አለመቻል መሆኑን ጠቅሳ፤ አብዛኞቻችን ከውጭ የመጣን ልብስ መልበስ እንፈልጋለን ትላለች:: ሁሉም ራሱን እንዲያይም ታሳስባለች::

ዲዛይነሯ እንደምትለው፤ አሁን ግን ብዙ ለውጦች እየመጡ ናቸው፤ ይህ ወቅት ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን አልባሳት እየወደዱ የመጡበት ጊዜ ነው:: ትላልቅ የሚባሉ ባለስልጣናትና አርቲስቶች ጨምሮ ታዋቂ ሰዎች የፋሽን አልባሳትን በመልበስ ትላልቅ ፕሮግራሞች ላይ በመገኘት ማበረታት ጀምረዋል ስትል ትናገራለች::

አንዳንዴ ከቻይና በጋርመንት ደረጃ በብዛት ተመርቶ የሚመጣን ልብስ መግዛት በዋጋ ቅናሽ ሊያስገኝ ይችል ይሆናል የምትለው ዲዛይነሯ፤ እኛ አገር ደግሞ ባማረ ዲዛይን ጥራት ያለው ልብስ ሠርቶ ለማቅረብ የኅብረተሰቡ ግንዛቤ መስፋትና መክፈል ያለበትን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለበት ትላለች:: የአገር ውስጥ ሲባል ያለው አመለካከትና የሚሰጠው የዋጋ ግምት ዝቅተኛ መሆን የለበትም፤ መራከስም የለበትም:: ዘርፉ ራሳችንን ካስከበርን ነው ማደግ የሚችለው ትላለች::

ከዚህ ባሻገር የፋሽን ተደራሽነትን በማስፋት ረገድ ሚዲያ ትልቅ ሚና እንዳለው የምትገልጸው ዲዛይነሯ፤ ፋሽን እይታ ነው፤ በአይን የምናየው ነገር በጫማ፣ በልብስ፣ በሜካፕ እና በማንኛውም ነገር ሊገለጽ የሚችል በመሆኑ ሲታይና ሲወደድ ተደራሽነቱ ሊሰፋ ይችላል:: ኅብረተሰቡም በአገራችን አልባሳት እንድንኮራ ሊያበረታታን ይገባል ነው የምትለው፤ የፋሽን ላይ የምንሠራ ባለሙያዎችም እርስ በርስ እየተበረታታን ከሄድን የማናድግበት ሁኔታ የለም ትላለች::

ዲዛይነር ሀና ኃይሌ በበኩሏ ውበትና ፋሽን ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች መሆናቸውን ገልጻ፤ ፋሽን ላይ ትኩረት አድርጎ ተሠርቶ ውበት ላይ ካልተሠራ ትርጉም የለውም ነው የምትለው:: ውበት ላይ የመሥራትን አስፈላጊነትም ጠቁማለች::

የፋሽን ሙያው እንዲያድግ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት እንደሚያስፈልግ የምትገልጸው ሀና፤ የውበትና የሙያ ማሰልጠኛ ተቋም በማቋቋም የወንድና የሴት ፋሽንን በዘመናዊ፣ ባህላዊ መልኩ እያስተማረች ፋሽንን ተደራሽ በማድረግ ላይ ትገኛለች::

የፋሽንን ተደራሽነት ለማስፋት በተማሪዎች ምረቃ ቀን እያንዳንዱ ተማሪ ሥራውን መድረክ ላይ እንዲያቀርብ ዕድሉን ይሰጠዋል ነው ዲዛይነር ሀና የምትለው፤ በዚህ ያለፉ ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ ልብሶችን ዲዛይን እያደረጉ ውጤታማ የሆኑ፣ የየራሳቸውን የፋሽን ሥራ የጀመሩ እና በፋሽን ዙሪያ የሚሠሩ ተማሪዎች እንዳሉም ትገልጻለች::

በአሁኑ ሰዓት ሙያው በጣም ተፈላጊ ስለሆነ ተማሪዎቻችንን ከብዙ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት የራሳቸውን መክፈት የሚፈልጉ እንዴት መክፈት እንዳለባቸው ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል:: በዚህ መንገድ ሁሉም ሙያውን የተማሩ በሙያው እንዲሰማሩ ስለሚደረግ ተምሮ ጨርሶ የሚቀመጥ አይኖርም ትላለች::

ቀደም ሲል ፋሽንም ሆነ ውበት ሲባል ምን ትኩረት አይሰጠውም፤ አማራጭ ሲታጣ የሚገባበት ዘርፍ አድርጎ የማሰብ የአመለካከት ችግር ይስተዋል እንደነበረ ትጠቅሳለች:: ፋሽን ለመማር በቅድሚያ የሚያስፈልገው ፍላጎት መሆኑን የምትገልጸው ሀና፤ አሁን የሰው ፋሽን የመማር ፍላጎት እየጨመረ ዲግሪና ማስተርስ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በተጨማሪነት እየተማሩት እንደሚገኙም ጠቅሳለች::

‹‹ውስጤ የነበሩ የምፈጥራቸውና ዲዛይን የማደርጋቸው ነገሮች እኔ ጋ ብቻ እንዲቀሩ ስላልፈለግኩ ነው ወደ ማስተማሩ ሥራ የገባሁት›› የምትለው ሀና፤ የማስተማር ሥራ ከጀመረች 15 ዓመታትን እንዳስቆጠረችም ትናገራለች:: በተለይ ሴቶች ላይ ብዙ መሥራቷን ገልጻ፤ በዘርፉ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ብዙ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ተግዳሮት ገጠሞኛል ብሎ ሥራ ማቆም ግን አይታሰብም፤ መቀጠል ያስፈልጋል ስትል አስገንዝባለች::

# ትዝብት/ ማረፊያ

## አንዳንዴ በጉዟችን ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

በቀኑ የሥራ ውሎ የተዳከመው ሠራተኛ ወደ ሰፈሩ የሚያደርሰውን ትራንስፖርት መጠበቅ ይዟል:: አብዛኛው የመንግሥት ሠራተኞችን አውቶቡስ የሚጠብቅ ነው:: የተቀረው የታክሲ ሰልፍ ይዞ ከወረፋው በተጠንቀቅ ቆሟል:: የሰሞኑ ዝናብ እንደልማዱ ‹‹መጣሁ›› እያለ ማስፈራራት ጀምሯል:: በስፍራው የቆምን አንዳንዶች ሰማዩን አንጋጠን እናያለን:: ካሁን አሁን ዳመናው ዝናብ ሆኖ ጉድ እንዳይሠራን ሳንፈራ አልቀረንም::

ደግነቱ በስሱ የጀመረው ካፊያ ብዙ አልቆየም:: እንዳመጣጡ ጥቂት ኅብኝቶን አልፎን ሄዷል:: የአውቶቡሱ ሰልፍ ቀስ በቀስ ተቀጣጥሎ አስፓልቱን ሊሻገር ነው:: ለዓይን የዘገየው ሰማያዊ አውቶቡስ እስካሁን ብቅ አላለም:: ጊዜው እስኪደርስ የሞባይሉን ሰዓት የሚቆጥረው ተሳፋሪ መበርከቱን አስተዋልኩ:: የልምድ ሆኖ እንጂ ሁሉም መነሻ ሰዓቱን ያውቀዋል::

ከሰልፈኞች መሀል አንዳንዱ አስር ሰዓት ሳይሞላ ከሥራው የወጣ ነው:: የአውቶቡሶች መንቀሳቀሻ ሰዓት ቢታወቅም ቀድመው መሰለፍ ሱስ የሆነባቸው ሞልተዋል::

ከቆምነው መሀል አብዛኞች ለመሄድ የቸኮሉ ይመስላል:: ያም ቢሆን ሾፌሮቹ ከሰዓታቸው ቀድመው አያሳፍሩም:: ይሄ እውነት ቢታወቅም አንዳንዶች መቁነጥነጥ፣ መጣደፍ ልማዳቸው ነው:: መቆም መቀመጡ የሰለቻቸው ጥቂቶች ቶሎ ተሳፍረው ለመሄድ ይቸኩላሉ:: እኔም ብሆን ስሜቱ ሳይጋባብኝ አልቀረም:: በየአፍታው ዓይኔን እየጣልኩ ማንጋጠጡን ይዣለሁ::

አሁን ጥቂት አውቶቡሶች መታየት ጀምረዋል:: አጠገባችን ሲደርሱ የያዙትን ይዘው እብስ ይላሉ:: የእኛው ሰማያዊ ፈረስ እስካሁን አልመጣም:: ሁላችንም በእጆቻችን መታወቂያዎች ይዘን እየጠበቅን ነው:: ጥቂት ደቂቃዎች አለፍ እንዳሉ ሲጠበቅ የነበረው አውቶቡስ ከች አለ:: ወዲያው በሁሉም ሰው ገጽታ የእፎይታ ፈገግታ ተስተዋለ::

ከሠራተኞች የተመረጠው ቋሚ አስተባባሪ መታወቂያ እያየ ለማስገባት ስፍራውን ይዟል:: ተሳፋሪው አንድ በአንድ ወደውስጥ መግባት እንደጀመረ አንዳንዶቹ ሲያጉረመርሙ ተሰማኝ:: ቀደም ሲል በቦታው ያልነበሩ ሁለት ሰዎች በ‹‹እንግባ አትገቡም›› ውዝግብ እየተጨቃጨቁ ነው::

አብዛኛው ሰልፈኛ ጣልቃ ገብቶ ሁለቱን ሴትና ወንድ እየገሰጸ ነው:: እውነት ለመናገር እኔም ብሆን ሰዎቹን አስቀድሜ አላየኋቸውም:: ቆይታዬ ጥቂት ባለመሆኑ መኖር አለመኖራቸውን ለመለየት አልቸገረኝም:: ከየት እንደመጡ ባላውቅም ‹‹እዚሁ ነበርን ሲሉ መከራከራቸው አሳፍሮኛል:: አንዳንዴ እንዲህ ዓይነት ደፋሮች አይጠፉም:: ዓይናቸውን በጨው አጥበው ከፊት ለመቅደም የሚያህላቸው የለም::

ለእንዲህ ዓይነቶቹ በይሉኝታ ይለፍ የሚሰጧቸው እንዳሉ ሁሉ አመናጭቀውና አዋርደው የሚያስወጧቸው አይጠፉም:: የሁለቱ ሰዎች ዕጣ ፈንታም ከዚህ አላለፈም:: አስቀድመው በስፍራው እንዳልነበሩ ተመስክሮባቸው ወደመጡበት ተመልሰዋል::

ድርጊታቸው እያስገረመኝ ወደውስጥ ማለፍ ጀምሬያለሁ:: ጥሎብኝ የምመርጠው ቦታ የጥጉን አቅጣጫ ነው:: አጋጣሚ ሆኖ ለዛሬ በጥግ ያሉት ወንበሮች በሙሉ ተይዘዋል:: ክፍት፣ ድብር አለኝ:: ሁሌም በመስታወቱ በኩል መቀመጥ ምቾት አለው:: ይህን የምናውቅ አብዛኞቻችን እነዚህን ቦታዎች እንመርጣለን::

ሰዓቱ ሲደርስ የሰፈራችን አውቶቡሱ ተንቀሳቀሰ:: ወንበር የያዘው እንዳለ ሆኖ ቆሞ ለመሄድ የተዘጋጀው ጥቂት አልሆነም:: ጥቂት አለፍ እንዳልን ያቆመ የመሰለው ዝናብ ማካፋት ጀመረ:: በዚህ ብቻ አልበቃውም:: መጠኑን ጨምሮ ያወርደው ጀመር:: በዚህ ከቀጠለ ሰበብ ፈላጊው መንገድ መዘጋጋቱ አይቀረም:: እኛስ ወንበር ይዘናል :: ‹‹ይብላኝ.›› ቆመው ለሚጓዙት:: አሳዘኑኝ::

ምስጋና ለሚገባቸው ሁሉ ይሁንና ይህ የመንግሥት ሠራተኞች አውቶቡስ ያላቃለለው የለም:: ተጠቃሚውን ከእንግልት ወጪ ታድጓል:: ሁሉም በጊዜ ወጥቶ ለሥራውና ለቤቱ እንዲደርስ አግዟል:: ይህን እያሰብኩ ዓይኖቼን ወደውጭ ወረወርኩ:: በርካታ ታክሲ ጠባቂ ዝናብ እየደበደበው ቆሟል:: የጫፉን መጨረሻ በወጉ ያላየሁት ረጅሙ ሰልፍ ማብቂያ ያለው አይመስልም::

ጉዞ የቀጠለው አውቶቡሳችን በጀመረው ፍጥነት ላይ ነው:: የባስ ካፒቴናችን እንደተለመደው በየምክንያቱ መነጫነጭ ይዘዋል:: ለምን እንደሆነ ባላውቅም ለመቆጣት ሰበብ አያጡም:: ሲሻቸው ከተሳፋሪው ጋር ሙግት ይዘው ይጋጫሉ:: ሲላቸው ደግሞ አንገታቸው አውጥተው ከሌሎች ሾፌሮች ጋር ይሰዳደባሉ::

ከሁሉም ግን አንድ ማለዳ የሆነውን እውነት ፈጽሞ አልረሳም:: በጠዋቱ ከቤት ወደሥራ መንገድ የጀመረው ሠራተኛ በካፒቴናችን ይሁንታና ምሪት እየተጓዘ ነው:: ጊዜው ባለመርፈዱ መንገዱ ነፃ ነበር:: እንዲህ ሲሆን በጊዜ ለመድረስ አይቸግርም:: ትልቁ ሾፌራችን ግን ዛሬም መንገዱ የጠበባቸው ይመስላል:: በቅርባቸው ያሉ ትናንሽ መኪኖችን በ‹‹አትድረሱብኝ›› ጡሩንባ እያንባረቁ መድረሻ አሳጥተዋቸዋል::

አንዳንድ ትናንሽ መኪኖች የአውቶቡሱን ግዝፈት እያዩ ጥግ ይይዛሉ:: ሌሎች ደግሞ መንገዳቸውን ጠብቀው በወጉ ይጓዛሉ :: ቁንጥንጡ ሾፌር ይህ ዓይነቱ እውነት ሁሌም ያናድዳቸው ይመስላል:: መንገዱ የጋራ እንዳልሆነ ‹‹የእኔ ብቻ ይሁን›› ማለትን ለምደዋል::

የዚያን ዕለት ማለዳም የሆነው እንዲሁ ነው:: አንድ መለስተኛ የጭነት መኪና ከጎናቸው ቆሞ ይቆይና ቀድሚቸው ያልፋል:: አስቀድሞ ቦታ እንዲለቅላቸው ሲጋፉት የቆዩት ካፒቴን ታዲያ እልህ ይይዛቸዋል:: መሪውን እየደበደቡ፣ አንገታቸውን እያወጡ እንደልማዳቸው አንባረቁ::

ጥቂት ቆይቶ ጆሮ ጭው የሚያደርግ ስድብ ከሁላችን ዘንድ ደረሰ:: የሬዲዮው ድምጽ ከፍ ያለ ቢሆንም አስደንጋጩ ቃል ጎልቶ ለመሰማት ኃይል አላጣም:: ክፉ ቃልና ክፉ ሽታ ቶሎ ለመድረስ ይፈጥናል ልበል? ዞር ብዬ የሌሎችን ፊት ቃኘሁ:: አብዛኞቹ በሀፍረት እጃቸውን ከአፋቸው ጭነዋል:: መኪናው ርቋቸው ቢሄድም በዋዛ ሊተውት አልፈለጉም:: ሰውዬው ፍጥነት ጨምረው ከኋላው ተከተሉት::

ሁሉም በድንጋጤና ስጋት ተያየ :: ሾፌሩ ያሰቡት አልቀረም:: ከመኪናው እንደምንም ተሽሎክሉከው ደረሱበትና ከጎኑ ተገሸሩ:: አንዳንዶች ድርጊታቸውን መታገስ አልቻሉም:: ሰውዬው ባይሰሟቸውም በግልጽ ተቃወሟቸው::

የጭነት መኪናው ሾፌር ሮጦ ያልጠገበ ጎረምሳ ነው:: የእኛን መኪና እንዳየ ከሰውዬው ጋር የእልህ ጨዋታ ጀመረ:: አሁንም መንገዱን ላለመልቀቅ ተገዳደራቸው:: ምክንያት ፈላጊው ካፒቴን በንዴት እንደጨሱ መንቀሳቀስ የጀመረውን መኪና ተከተሉት:: በጣም እየፈጠኑ ነው:: ሁላችንም በጩኸት ተንጫጫን:: መኪናው ፍጥነቱን አልቀነሰም:: የሌባና ፖሊስ የሚመስለው አባሮሽ ዋና መንገዱን ለቆ ውስጥ ውስጡን ቀጠለ::

አሁን ጎረምሳው ሾፌር የደነገጠ ይመስላል:: መኪናውን በፍጥነት እያከነፈው ነው:: የሁላችንም ድንጋጤ ከቀድሞው ይበልጥ አይሏል:: ሽማግሌው ደንታ አልሰጣቸውም:: ሾፌሩን ለመድረስ የእርምጃ ርቀት ቀርቷቸዋል:: ሁሉም ሰው ሁለቱ ቢገናኙ የሚፈጠረውን እያሰበ ተሳቀቀ ::

የፊትና ኋላው ግብግብ በአጭር ርቀት ቀጠለ:: ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ መልካም አጋጣሚው ተፈጠረ:: ለማቋረጥ በሁለቱ መካከል የገቡት ጥቂት መኪኖች ታሪክ ቀየሩ:: ተሯሯጮቹ ኃያላን ርቀታቸው ሰፍቶ በድንገት ተለያዩ:: ሽማግሌው ሾፌራችን ግዳይ አልቀናቸውም:: መሪውን እየደበደቡ ስድባቸውን ቀጥለው መንገዳቸውን ይዘዋል::

ጥቂት ስረጋጋ ያለሁበትን አካባቢ ቃኘሁ ከዚህ ቀድሞ ያልሄድንበት የውስጥ ለውስጥ መንገድ ላይ ነበርን:: ዞር ብዬ ሌሎችን አስዋልኩ በኀዘኔታና በሀፍረትና ድንጋጤ ተሸማቀዋል::

ይህ ዓይነቱን ድርጊት የለመደው ተሳፋሪ ከመታዘብ ውጪ አስተያየት ለመስጠት አይደፍርም:: ልናገር ቢል ደግሞ የሚደርስበትን አሳምሮ ያውቃል:: ነጭናጫውና ቁጡው ሾፌር ለእሱም የሚተርፍ የነገር ዱላ አያጡለትም:: ባጋጣሚ ዕለቱ እንዲህ ቢያልፍም ሊሆንና ሊከሰት የሚችለውን አደጋ መገመት አይቸግርም::

በእርግጥ እጅግ መልካም ሥነምግባር ያላቸው የአውቶቡስ ሾፌሮች አሉ:: በዚህ እውነታ ደግሞ አብዛኛው ተጠቃሚ ይስማማል:: እንደዛሬው ሳይሆን ከጥቂት ጊዜያት በፊት ለእንዲህ ዓይነቶቹ ልበ መልካሞች ሽልማትና ስጦታ ይበረከት ነበር:: እንዲህ ሲደረግ አብዛኛው ተሳፋሪ አይሰስትም፣ በራሱ ይሁንታ ተነሳስቶ አክብሮቱን ያሳያል::

ዛሬ ይህን ጉዳይ ሳነሳ መልካም ሥነምግባር ላላቸው በጎ ካፒቴኖቻችን ምስጋናንን በመቸር ነው:: እኛም በሥነምግባራቸው የሚታወሱ፣ በተባባሪነታቸው የሚሞገሱ፣ በሠሩት ድንቅ ተግባር ተቋማቸው ጭምር የሸለማቸውን ጀግኖች ሁሌም እናደንቃለን:: አሁንም በያሉበት ሰላማቸው ይብዛ:: አንዳንዴ ደግሞ በስንዴ መሀል እንክርዳድ አይጠፋምና ከትዝብቱ፣ ለእርምቱ ይህን ብለናል:: መልካም መንገድ ::

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ዛሬም በእኔ ስም አይሆንም

ሰሞነኛ አስደንጋጩ መርዶ የአማራ ብልጽግና ጽ/ቤት ኃላፊ የአቶ ግርማ የሺጥላ ግድያ ነው ። መርዶው ብዙኃኑን ያለልዩነት አሳዝኗል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም ፤ «ሐሳብን በሐሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው አካላት የወንድማችንን የግርማ የሺጥላን ነፍስ ነጥቀዋል። ልዩነትን በሠለጠነ መንገድ መፍታት ባህል በሆነበት ክፍለ ዘመን፣ በሐሳብ የተለየንን ሁሉ በጠመንጃ ለማሳመን መነሣት የጽንፈኝነት የመጨረሻው ጥግ ነው። ተወልዶ ባደገበት አካባቢ፣ ከእኛ የተለየ ሐሳብ ማሰብ አልነበረበትም ብለው የሚያምኑ ነውጠኛ ጽንፈኞች የፈጸሙት አስነዋሪና አሰቃቂ ተግባር፣ ጽንፈኝነትን በጊዜ ታግለን ካላስወገድነው ወደ መጨራረስ እንደሚወስደን ጉልሕ ማሳያ ነው።» በማለት አውግዘውታል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለም ፤«በዛሬው ዕለት ወንድማችን አቶ ግርማ የሺጥላ በሥራ ላይ በነበረበት በታጠቁ ኃይሎች ግድያ ተፈጽሞበታል። እንዲህ ዓይነት እብሪተኝነት ውድቀትን እንጂ ድልን አያጎናጽፍም። ጥፋትን እንጂ ሰላምን አይሰጥም። የሕዝባችን የቆየ መገለጫው ሥርዓታዊነት፣» በማለት ኮንነውታል። የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) በኀዘን መግለጫው፤ «በብልጽግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባል በነበሩት አቶ ግርማ የሺጥላ ላይ የተፈጸመውን የግድያ ጥቃት በጽኑ ያወግዛል፣ ጥልቅ ኀዘኑን ይገልጻል፣ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለሥራ ባልደረቦቻቸው እና ለመላው የአገራችን ሕዝብ መጽናናትን ይመኛል። » ካለ በኋላ በማስከተልም ፣ «የክልሉ መንግሥት አመራሮች ላይ ተደጋግሞ እየተፈጸመ ያለው የግድያ ጥቃት ክልሉን የቀውስ ማዕከል የሚያደርግ፣ የአገራችንን ሰላም እና መረጋጋት አደጋ ላይ የሚጥል የዜሮ ድምር ፖለቲካዊ ሽብር ውጤት በመሆኑ ድርጅታችን አብን በጽኑ የሚያወግዘው ወንጀል ነው። » ብሏል።

ባለፈው ሐሙስ ሰሜን ሸዋ መሀል ሜዳ ጎሳ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በጥይት የተገደሉት የአማራ ብልፅግና ፓርቲ ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ዘርፍ ኃላፊ በመሆን በታኅሣሥ 1988 ዓ.ም የአመራርነት ሥራን የጀመሩ። በዚያው ዓመት ሐምሌ ወር ላይ የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሆነው ተሹመዋል። በዚህ የኃላፊነት ቦታ ላይም ለሰባት ዓመት ገደማ ቆይተዋል። በጥር 1995 ዓ.ም ከወረዳ ወደ ዞን በመሸጋገርም፤ የቀድሞው ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የሰሜን ሸዋ ዞን ጽሕፈት ቤት የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ መሆን ችለዋል።

ለአንድ ዓመት ገደማ በዚህ ኃላፊነት ቦታ የቆዩት አቶ ግርማ፤ በጥር 1996 ዓ.ም የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ሹመት አግኝተዋል። በ2002 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከደብረብሃን ዩኒቨርሲቲ በምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚክስ) ትምህርት ዘርፍ ያገኙት አቶ ግርማ፤ በዚያው ዓመት የሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር የሕዝብ ግንኙነት አማካሪ ሆነዋል። እስከ ግንቦት 2003 ዓ.ም ድረስ በዚሁ ቦታ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ፤ የሰሜን ሸዋ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ ሆነው ተሹመዋል። በምክትል አስተዳዳሪነት ደረጃ ለአራት ዓመታት ገደማ የቆዩት አቶ ግርማ፣ ዞኑን የመምራት ኃላፊነት በመስከረም 2008 ዓ.ም ተረክበዋል። የሰሜን ሸዋ ዞንን ለሁለት ዓመት ገደማ የመሩት አቶ ግርማ፤ በ2012 ዓ.ም በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ይዘዋል። በዚህ አጋጣሚ ለቤተሰባቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው መጽናናትን እመኛለሁ። አብን በኀዘን መግለጫው እንዳወሳው እኔም ወደ ኋላ መለስ ብዬ ከዚህ ቀደም ማለትም ከአራት አመት በፊት በአማራ አመራሮች ላይ የተፈጸመውን ግድያ ለማውገዝ ያጠናቀርሁትን መጣጥፍ እንድመለስበት ምክንያት ሆኖኛል።

አዲሱ Irish Republican Army IRA በ2019 ዓ.ም በወርሀ ግንቦት በለንደንዴሪ በጠራው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ አንድ ንክ አንጋች ለፖሊሶች የተኮሳት ጥይት የ29 አመቷን ጋዜጠኛ ሊራ ማኪ ሥራ ላይ እንዳለች በአጭር ቀጫት:: BBCን ጨምሮ ታዋቂ ዓለምአቀፍ ሚዲያዎች ሊራ ስለምትወደው ሙያ መስዋዕት መሆኗን ሳያሰልሱ ዘገቡ:: የከተማዋ ነዋሪዎችም በድርጊቱ ክፉኛ በመቆጣት ተጠርጣሪውን አሳልፈው ከመስጠት አልፈው «በእኛ ስም አይሆንም ! » የሚል መፈክር አንግበው እንደገና አደባባይ ወጥተዋል:: አዎ ! ጋዜጠኛ ሊራን የገደላት በጥላቻ ተገፋፍቶ ታውሮ እንጂ ለእኛ ወይም ለIRA ብሎ አይደለም በማለት እዚያው በጠበልህ ብለውታል:: እኔም እንደገና በእኛ ስም አልሆነም እላለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የእነ አምባቸውን ግድያ አስመልክተው በወቅቱ ፤ «አምባቸውን እንኳን በጥይት ደብድቦ ለመግደል ለመቆጣት እንኳ የሚሰሰትለት ሰው ነው::» ብለዋል:: ስለ ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጄነራል ሰዓረ መኮንንም «ኢትዮጵያዊነትን፣ ዴሞክራሲያዊ ለውጥን በመደገፉ እንደ ገና ዳቦ ከታችና ከላይ እሳት እየነደደበት የነበረን አገር ወዳድ ጀግና መግደል፤ » ምን ያህል አረመኔአዊ ድርጊት እንደሆነ ተናግረዋል::

> **አሜሪካውያን መብታቸውን ተጠቅመው በነፃና ዴሞክራሲያዊ ሂደት በድምጻቸው የሾሙት መንግሥት እንኳ ከአንዴም ሁለት ሦስቴ ያሰመሩለትን ቀይ መስመር ጥሷል ብለው ባመኑ ጊዜ አደባባይ ወጥተው «በስማችን አይሆንም፡፡ » ብለውታል**

ወደ ዛሬው ነቃሽ መጣጥፌ ስመለስ ፤ Not In Our Name « በእኛ ስም አይሆንም » በአሜሪካ በመስከረም 1 1993 ዓ.ም በተለምዶ 9/11 ላይ አልቃይዳ በአሜሪካ ላይ የሽብር ጥቃት መፈፀሙን ተከትሎ አሜሪካ አፍጋኒስታንን ጨምሮ በኢራቅና በቀጣናው ያወጀችውን ጦርነት ዜጎች በመቃወም «በእኛ ስም አይሆንም » በማለት እ አ አ በየካቲት 23 2002 የተቋቋመ ሕዝባዊ ንቅናቄ ነው:: ቻርሊ ሀደን የተባለ ታዋቂ አቀንቃኝ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ቶኒ ብሊየር ኢራቅ ላይ ለፈፀሙት ወረራ ለፍርድ ይቅረቡ የሚል መልዕክት ያለው " Not In Our Name " የተሰኘ የዘፈን ሲዲ መልቀቁ ንቅናቄውን ይበልጥ አኸዝቦታል::

በአገራችን በተለይ ካለፈው አምስት አመት ወዲህም ሆነ ከዚያ በፊት እዚህም እዚያም በዘውግ በማንነት በጎሳ ስም ዜጎች እየተገደሉ እየተፈናቀሉ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት እየተዘረፈ የዜጎች በሰላም ወጥቶ የመግባት የመንቀሳቀስ መብት እየተገደበ የአገር የግዛት አንድነት አደጋ ላይ እየወደቀ የሕግ የበላይነት እየተደፈቀ ከፍ ሲልም እንደ አገር የመቀጠል ጉዳይ ጥያቄ ላይ እየወደቀ ነበር :: በሶማሊያና በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉልና ኦሮሚያ፣ በአማራና በቤኒሻንጉል፣ በአማራና በትግራይ ፣ በጉጂና በጌዲዎ ፣ በቅማንትና በአማራ የተከሰቱ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን በአብነት ማንሳት ይቻላል:: በጅግጅጋና በምዕራብ ኦሮሚያ የአገሪቱን የግዛት አንድነትና ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣሉ ለመስማት የሚዘገንኑ የሰብዓዊ መብት ጥቃቶችና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የጅምላ ግድያዎችን ዛሬ ድረስ የምናስታውሳቸው ዋና ዋና ሰቆቃዎች ናቸው::

ሆኖም እነዚህን ሁሉ ጥቃቶች፣ ግድያዎች፣ ማፈናቀሎች፣ ጭፍጨፋዎች፣ ዘረፋዎች በእኛ ስም ጥቂት ፅንፈኞች የፈፀሟቸው ናቸው :: አዎ ! በእኛ በኢትዮጵያውያን ( በአማራ፣ በኦሮሞ፣ በትግራዋይ፣ በሶማሊያ፣ በሲዳማ፣ በጌዲዎ፣ በጉጂ፣ በጉምዝ በበርታ በቅማንት፣ በሽካ ስም ) የተፈፀሙ ናቸው:: የእኛን የብዙኃኑን ይሁንታ ድጋፍ ሳያገኙ በእኛ ስም ሲፈፀሙ «በእኛ ስም አይሆንም» አይደረግም:: አላልንም:: ይህ ዝምታ ቸልታ ነገ በፍትሕ አደባባይ ባያስጠይቀንም በትውልድ በታሪክ ማስጠየቁ ግን አይቀርም :: ትናንት ክልሌን ለቀህ ውጣ ተብሎ የመጀመሪያው ወገናችን ሲፈናቀል እኛ ብዙኀኖች «በእኛ ስም አይሆንም :: » አፈናቃዩ እኛን አይወክልም ብለን ከጅምሩ አምርረን አቋማችንን ብናሳውቅና ብንታገል ኖሮ ኋላ ላይ ሚሊዮኖች ባልተፈናቀሉ:: ወሰኔን ገፍተሀል በሚል የአንድ ክልል ሚሊሺያ ከሌላው ጦርነት ገጥሞ ንፁሀንን ሲገደሉ ሲያቆስሉና ሲያፈናቀሉ «በእኔ ስም አይሆንም :: » ብንል እስከ ዛሬ በመቶዎች አልያም በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ባልተገደሉ::

ስለሆነም በአንድም በሌላ በኩል በአገራችን ለተስተዋሉ ችግሮች ለተደቀኑ አደጋዎች እጃችን አለበት:: በትውልድም በታሪክም ተጠያቂ ነን:: በማህበራዊ ሚዲያዎች የጥላቻ የጎሰኝነት የቂም በቀል መርዘኛ ፍላፃዎች በስማችን ሲንበለበሉ ከፍ ሲልም የግጭት የጦርነት የመገንጠል ነጋሪቶች በስማችን በማንነታችን በፌስ ቡክ ሲጎሸሙ «በእኛ ስም አይሆንም:: » ብለን በአደባባይ ባለመጮሀችን በሀፍረት አንገታችን የሚያስደፉ ነውሮች ተፈፅመዋል:: እየተፈፀሙም ነው:: በስማችን በማንነታችን የሚነዛ የበሬ ወለደ ሀሰተኛ የተዛባ መረጃን የደባ የሴራ ፖለቲካን «በእኔ ስም አይሆንም:: » ለማለት አንደበታችንን ማን ሸበበው ? ብዕራችንን ማን አዶሎደመው ? የስልኮቻችንን የኮምፒዩተሮቻችን ኪቦርድ ማን ቆለፈው ? የቅስም ቀውሱን ድንዛዜውን ማን አጋባብን ? አንገታችንን ማን አደነደነው ? ልባችንን ማን ደፈነው ? ይሄ ሁሉ ኬሬዳሽነት ከየት መጣ ? ስንል ቆመን የምናስብበት ወደቀልባችን የምንመለስበት ወሳኝ ሰዓት ላይ እንገኛለን::

ጥቂቶች ስማችንን ማንነታችንን ነጥቀው በስማችን በማንነታችን የሚፈፅሙትን ግፍ ወንጀል በድፍረት ከአሁን በኋላ በቃ ! Enough is Enough ! «በእኛ ስም አይሆንም :: » በማለት የተነጠቅነውን ስማችንን ማንነታችንን ምርኳችን ካላስመለስን እንደ አገርም ሆነ እንደ ሕዝብ የተደቀነብንን አደጋ በቀላሉ መሻገር ይቸግረናል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳስጠነቀቁት፤ «ጽንፈኝነትን በጊዜ ታግለን ካላስወገድነው ወደ መጨራረስ እንደሚወስደን ጉልሕ ማሳያ ነው ።»

እንዲሁም በፌዴራል በክልል በግልና በድርጅት መደበኛ ሚዲያ ማለትም በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ( በጋዜጣ ፣ በሬዲዮ ፣ በቴሌቪዥን ) በማንነታችን በስማችን ከአንድነት ይልቅ ልዩነት ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ከእርቅ ይልቅ ጥል ከመተባበር ይልቅ መፎካከር ከመነጋገር መኳረፍ ከመቀባበል መገፋፋት ሲቀነቀን ሲለፈፍ ሰምተን እንዳልሰማን አይተን እንዳላየን አንብበን እንዳላነበብን ያለፍነው ጽንፈኝነትና አክራሪነት ዛሬ በአገራችን ለተቀለሱት የጭፍን ጥላቻ የቂም የዘውጌ'ዊነት የደባ ፖለቲካ የመጠራጠር የመጠላለፍ መሪን የመብላት ጎጆዎች ዋልታና ማገር አቀብለዋል::

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም መጀመሪያ በባህር ዳር በኋላ በአዲስ አበባ የተፈፀመው ጅብደኛ ግድያ የዝምታችን የድንዛዜአችን የግዴለሽነታችን የዕንዝህላልነታችን ከፍታ ጡዘት climax ማረጋገጫ ማሳያ ነው:: የቀጣይ አካሄዳችን የታሪካችን ወሳኝ መታጠፊያ ነው:: ከእያንዳንዱ የግጭት መካረር ጡዘት በኋላ የሁኔታዎች መቀየር የግድ መሆኑን መቀበል ተፈጥሮአዊም ሰዋዊም ነው:: ስለሆነም ድምጻችንን ከፍ አድርገን «በእኛ ስም አይሆንም:: » የምንልበት ቀን አፍጥጦ ደጃችን ላይ ደርሷል:: ቀኑን በአግባቡ መጠቀምም ዘመኑን የሚመጥን የሚዋጅ እርምት በጊዜ የለም ስሜት መውሰድ ደግሞ የቀረን ብቸኛ ካርድ ነው::

ከላይ ለማሳየት እንደሞከርሁት በስማችን በማንነታችን የሚነዙ ጽንፈኝነቶች፣ አክራሪነቶች፣ የጥላቻ መርዞች የደባ ፖለቲካ ሴራዎች የሚንበለበሉ የቂም ፍላጻዎች በጊዜ ባለመመከታቸው ዛሬ ጎልምሰው ተቋማዊ፣ ሥርዓታዊ ፣ መዋቅራዊ ሆነዋል :: ስለሆነም የሚመጥን ሕጋዊና ተቋማዊ እርምጃ የመውሰጃ ትክክለኛው ጊዜ ላይ ደርሰናል:: ኧረ እንዲያውም አርፍደናል::

አሜሪካውያን መብታቸውን ተጠቅመው በነፃና ዴሞክራሲያዊ ሂደት በድምጻቸው የሾሙት መንግሥት እንኳ ከአንዴም ሁለት ሦስቴ ያሰመሩለትን ቀይ መስመር ጥሷል ብለው ባመኑ ጊዜ አደባባይ ወጥተው «በስማችን አይሆንም:: » ብለውታል :: አሜሪካ ተገድጄ ገባሁበት በምትለው 2ኛው የዓለም ጦርነት በጃፓን የሔሮሽማና ነጋሳኪ ከተሞች የመጀመሪያውን የአቶሚክ ቦምብ ጥቃት ሲፈፅም:: በአሜሪካ የሚገኙ ጃፓናውያንንና ትውልደ ጃፓን አሜሪካውያንን ለደህንነቴ ያሰጉኛል በማለት በማጎሪያዎች ሰብስቦ ሲያጉር:: ቬትናምን ሲወር:: የመስከረም 1ዱን የአልቃይዳ የሽብር ጥቃት ተከትሎ ጆርጅ ደብሊው ቡሽ «ከእኛ ጎን ትቆማላችሁ አልያም በእኛ ላይ ተነስታችኋል:: » በማለት ኢራቅን አፍጋኒስታንን በወረሩ ወቅት አብዛኛው አሜሪካዊ አደባባይ በመውጣት ድምፁን ከፍ አድርጎ «በእኛ ስም አይሆንም:: » በማለት በመንግሥታቸው ላይ ጫና በመፍጠር ለውጥ አምጥተዋል::

ወደ አገራችን ስንመጣ በእኛ ላይ ራሳቸውን በጎበዝ አለቅነት የሾሙ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች፣ የመብት ወትዋቾች ፣ ጦማሪያን ፣ ሚዲያ ተብዬዎች በኢትዮጵያዊነታችን አልያም በማንነታችን ስም ትርምስ ቀውስ የእርስ በርስ ግጭት ጦርነት ዕልቂት ሲደግሱልን ዝምታን በመምረጥ የጥፋታቸው ተባባሪ እየሆንን ነው:: ትናንት በመሐል ሜዳ ከዚያ በፊት በአዲስ አበባ ፣ በጅግጅጋ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ በስማችን ለተፈፀመው ግፍ ፣ ሞት ፣ መቁሰል ፣ መነቀል በዝምታ ስለተመለከትን ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን :: አዎ ! ወደድንም ጠላን ከግፈኞች ይልቅ ግፉ ሲፈፀም አይተው እንዳላዩ ሰምተው እንዳልሰሙ ሆነው ዝምታን የመረጡም ተጠያቂዎች ናቸው እንደሚባለው ከላይ እንዳልሁት በቀጣይ ትውልድ ታሪክ ይጠይቀናል ::

**«ዛሬም በእኔ ስም አይሆንም !»**

**ሻሎም ! አሜን ።**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የዘንድሮ የበልግ ወቅትና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራዎች

## . ከበልግ ወቅት 24 ሚሊዮን ኩንታል ሰብል ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ ነው

## . የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት አዝመራ የመሰብሰቡ ሥራ ተጠናክሯል

ኃይሉ ሣህለድንግል



**52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት እቅድ የተያዘለት የዘንድሮው የበጋ መስና ስንዴ ልማት አዝመራ እየተሰበሰበ ነው**

የኢትዮጵያ የሰብል ልማት በዋናነት በመኸርና በበልግ ወቅቶች ይከናወናል፤ ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ሥራም እነዚህን ወቅቶች ተቀላቅሏል:: መንግሥት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ይበልጥ ለማሳደግ በሦስቱም የግብርና ወቅቶች ላይ ሰፋፊ እቅዶችን ይዞ በትኩረት ይሠራል::

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ጭምር መካሄድ በጀመረው በዚህ የግብርና ሥራ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እየታቸለ ነው:: በግብርና ሚኒስቴር የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተመለከተውም ይህንኑ ይጠቁማል::

በሪፖርቱ ላይ እንደተጠቆመው፤ በበጀት ዓመቱ በ2014/2015 የምርት ዘመን በሰብል ልማት በአነስተኛ አርሶ አደሮች በመኸር 13 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በማልማት 472 ሚሊዮን ኩንታል ለማምረት ታቅዶ 14 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር (ከመቶ ፐርሰንት በላይ) መሬት በሰብል መሸፈን ተችሏል:: አዝመራው ከተሰበሰበው 14 ነጥብ 43 ሚሊዮን ሄክታር መሬትም 480 ሚሊዮን ኩንታል (ከመቶ ፐርሰንት በላይ) ምርት ተገኝቷል:: ከዚህ ውስጥ የአነስተኛ አርሶ አደሮች የአዝርዕት ሰብል 13.4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 14 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል:: ከዚህም 393.3 ሚሊዮን ኩንታል (99.9 በመቶ) ምርት ማግኘት ተችሏል::

ግብርናው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብቻ የሚሠራበት አይደለም፤ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት አስተዋጽኦ በማድረግም ይታወቃል፤ ከግብርናው ዘርፍ በርካታ ምርቶች ለውጭ ገበያ እየቀረቡ ሲሆን፣ ዘንድሮ ደግሞ የስንዴ ምርትም የውጭ ገበያውን ተቀላቅሎታል:: ከውጭ የሚገባ የስንዴ ምርት በአገር ውስጥ መተካትም ተችሏል::

እንደሚታወቀው ያለንበት ወቅት የበልግ እርሻ የሚካሄድበት ነው:: የበልጉ ዝናብ ወራትን ለዘለቀ ጊዜ እየጣለ ይገኛል:: የበልግ አብቃይ አካባቢ አርሶ አደሮችና ሌሎች የግብርናው ዘርፍ ተዋንያንም በመኸር እና በበጋ መስኖ ወቅት እየተደረገ እንዳለው ሁሉ በዚህ የምርት ወቅትም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሰፊ ርብርብ እያደረጉ ናቸው::

በልግ አብቃይ የሆኑት የአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት በሰፊ የግብርና ሥራ ላይ ተጠምደዋል፤ እንደ አገርም በእነዚህ አካባቢዎች ለሚደረገው የበልግ እርሻ ሥራ ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ ነው ወደ ሥራ የተገባው::

በሌላ በኩል ደግሞ ወቅቱ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚካሄድበትና አዝመራ መሰብሰብ የተጀመረበትም ነው:: የመኸር እርሻ የሚጀመርበትም ወቅት ነው:: በተለይ እየጣለ ያለው ዝናብ ለበልጉ ወቅት ብቻ ሳይሆን የመኸር እርሻውን ለመጀመር ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ ሊባል የሚችል ነው:: የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው በሰጡን ማብራሪያ እንደ አገር በእነዚህ ሦስት የግብርና ሥራዎች ላይ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል::

### የበልግ ወቅት

እንደ አቶ ከበደ ገለጻ፤ እንደ ግብርና ሚኒስቴር በእዚህ የበልግ ወቅት የታቀደው ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ነው:: እስከ መጋቢት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ታርሷል:: ከዚህ ውስጥም አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታሩ በዘር ተሸፍኗል:: ቀሪዎቹ ደግሞ በዚህና በቀጣዩ ወራት ይሸፈናሉ::

በእቅድ ለማልማት ከተያዘው መሬትም ወደ 24 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ሥራ አስፈጻሚው ይገልጻሉ:: በእነዚህ በልግ አብቃይ አካባቢዎች በዋናነት የሚመረቱት በቆሎ፣ ማሽላ ስንዴና ጤፍ መሆናቸውን አስታውቀው፣ ማሳዎቹም በእነዚህ የእህል ዘሮች እየተሸፈኑ መሆናቸውን ነው ያመለከቱት::

እሳቸው እንዳሉት፤ በተያዘው እቅድ መሠረት ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር በዘር ለመሸፈን ከተያዘው እቅድ፣ እስከ አሁን ባለው አፈጻጸም ወደ 64 በመቶውን በመዘር መሸፈን ተችሏል:: በቀሪዎቹ ወራትም (በሚያዝያ እና ግንቦት) የግብርና ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል፤ ምክንያቱም የግብርና ሥራ ከወቅት እና ከዝናብም ጋር የሚሄድ ስለሆነ በቀጣይ ደግሞ የቀረውን በእቅድ የተያዘ መሬት አርሶ፣ አለስልሶ በዘር ሸፍኖ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ይሠራል::

ይህን ለማድረግ ደግሞ ከክልል እስከ ዞን ወረዳ ድረስ ያለው ሠራተኛና አመራሩ ሁሉም በአገር ደረጃ በበልግ ወቅት የታቀደውን ምርት ለማግኘት በቅንጅት ርብርብ እያደረጉ ናቸው:: ይህ ሥራ በመኸርም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱም ተጠናክሮ ይቀጥላል:: የእነዚህ ሦስቱ የእርሻ ወቅቶች በተቀናጀ መልኩ መፈጸም የአገሪቱን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በምጣኔ ሀብቱ ላይ የሚኖረው ድርሻ ወሳኝ ይሆናል::

በአገሪቱ የበልግ ዝናብ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: በበልግ ዝናብ መዘግየትና መጥፋት የተነሳ ለድርቅ ተጋልጠው በቆዩ አካባቢዎች ሁሉ ጥሩ ዝናብ እንዳለ ተረድተናል ያሉት አቶ ከበደ፣ አርሶ አደሮቹን የመደገፍና የማቋቋም ሥራዎች በግብርና ሚኒስቴር በኩል በስፋት እየተካሄዱ ናቸው ሲሉም ጠቁመዋል:: ለሰዎች የቁሳቁስ፣ የምግብ፣ ለእንስሳትም የመኖ፣ የመድኃኒት አቅርቦት እየተደረገ ነው:: ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ በአጠቃላይ በሶማሌ፣ በኦሮሚያና ደቡብ ክልል በድርቁ የተነሳ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ግብርና ሚኒስቴር ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ድጋፍ አድርጓል ሲሉም አብራርተው፣ የባለሙያ ድጋፍ በማድረግ ላይም በስፋት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል::

ምክንያቱም ከዝናቡ ጋር ተያይዞ በሽታ እንዳይስከትና የበለጠ ጉዳት እንዳያደርስ የግብርና የእንስሳት ባለሙያዎች እዚያው በቅርበት ሆነው ይህን ድጋፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በቀጣይም ዝናቡ የሚጠናከር ከሆነ በዚህም ላይ በሰፊው ይሠራል ብለዋል::

### የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት

በሚኒስቴሩ የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ላይ እንደተመለከተው 2014/15 ምርት ዘመን በመስኖ አንድ ነጥብ ሰባት ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ሰብል ለማልማት ታቅዶ ሁለት ነጥብ ሁለት ሰባት ሚሊዮን ሄክታር (ከእቅድ በላይ) በዘር መሸፈን ተችሏል::

ከዚህ ውስጥ ከውጭ የሚገባውን የስንዴ ምርት በአገር ውስጥ ለመተካት የተቀመጠውን አገራዊ ግብ ለማሳካት የመስኖ ስንዴ ልማቱ /በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ፣ በሶማሌ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በአፋር ክልሎች/ እየተካሄደ ይገኛል:: በዚህም በአጠቃላይ አንድ ነጥብ ሦስት ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር በመሸፈን 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ታቅዶ አንድ ነጥብ ሦስት ስድስት ሚሊዮን ሄክታር /ከመቶ ፐርሰንት በላይ/ መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል::

ይህም አዝመራ በባህላዊና ዘመናዊ መንገድ እየተሰበሰበ ነው፤ በባህላዊ ዘዴ 274 ሺ 853 ሄክታር በዘመናዊ ዘዴ ደግሞ 62 ሺ 852 ሄክታር በድምሩ 337 ሺ 705 ሄክታር መሬት ላይ በበጋ መስኖ የለማ የስንዴ አዝመራ ተሰብስቧል፤ በዚህም 7 ሚሊዮን 849 ሺ441 ኩንታል ምርት ተገኝቷል:: በባህላዊ ዘዴ ከተሰበሰበው 274 ሺ 853 ሄክታር መሬት ላይ የተሰበሰበው ስንዴ ገና እንዳልተወቃ ሪፖርቱ ጠቁሟል:: የምርት መሰብሰቡ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል::

ከበልግ ዝናብ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ አካባቢዎች በደረሰ የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ ላይ ትንሽ ጉዳት የደረሰበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ዝናቡ አዝመራውን እንዳያበላሽ የመሰብሰቡን ሥራ አጠናክረን እንቀጥላለን ያሉት አቶ ከበደ፣ ስለዚህ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል እናገኛለን ብለን ያቀድነው ላይ ለመድረስ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል::

በደረሰ የበጋ መስኖ አዝመራ ላይ ዝናቡ ጉዳት እንዳያደርስ አርሶ አደሩ ቶሎ ቶሎ እንዲሰበስብ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም አቶ ከበደ አስታውቀዋል:: ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም የደረሰ የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ በዝናቡ እንዳይበላሽ አርሶ አደሩ በአስቸኳይ እንዲሰብሰብ እንዲደረግ በማህበራዊ ሚዲያ ገጾቹ እያሳሰበ ይገኛል ነው ያሉት::

ዝናቡ ወቅቱን ያልጠበቀ አይባልም፤ ወቅቱ የበልግ ወቅት ነው:: እኛ ደግሞ በመስኖ የዘራነው የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ አለ:: በእሱ ላይ የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ የደረሰውን ቶሎ ቶሎ የመሰብሰብ ሥራ እንዲሠራ ምክረ ሀሳብ እየተሰጠ ነው ሰሉ ገልጸዋል::

### የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት

ከግብርና ሥራዎቹ ጋር በተያያዘ መነሳት ያለበት ትልቁ ጉዳይ የግብአት አቅርቦት ነው:: አቅርቦቱን በሁለቱም የምርት ወቅቶች አርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያ እንዲጠቀም ተደርጓል:: በዚሁ መሠረት ለበልግ 533 ሺ 681 ነጥብ ሰባት ኩንታል ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ቀርቧል:: ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ደግሞ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል:: በድምሩ ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ጥቅም ላይ ውሏል::

በልጉን ስንጨርስ ወደ መኸር እንገባለን:: ወደ መኸር ስንገባ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስፈልገን ትልቅ ግብአት ማዳበሪያ መሆኑ ይታወቃል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ በዚህ መሠረት 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል:: የከረመ/ አገር ውስጥ የነበረ/ ወደ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል አለ:: በድምሩ 15 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለምርት ዘመኑ ጥቅም ላይ እንዲውል እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ከውጭ አገር የተገዛው 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የአፈር ማዳበሪያ ወደ አገር ውስጥ የማጓጓዝ ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ ናቸው:: በዚሁ መሠረት ከአምስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ የአፈር ማዳበሪያ ወደ አገር ውስጥ ማእከላዊ መጋዘን ገብቷል፤ ከዚያም ወደ ክልሎች፣ ክልሎች ደግሞ በማህበራትና ዩኒየኖች በኩል ወደ አርሶ አደሩ እንዲደርስ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል:: ይህም ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ ወደ አርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ::

በ2015/16 የምርት ዘመን ለየት የሚለው ነገር በማዳበሪያ ግዥው ላይ መንግሥት የ21 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉ ነው:: በዚህም የማዳበሪያ ዋጋ በአንድ ኩንታል የአንድ ሺ አምስት መቶ ስልሳ ብር ቅናሽ ይኖረዋል ማለት ነው:: ስለዚህ አርሶ አደሩ በአፈር ማዳበሪያ ግዥ በኩል ጫና እንዳይፈጠርበት በሚል መንግሥት የተወሰነ ኃላፊነቱን በመውሰድ ድጎማ አድርጓል:: ለማዳበሪያ የተደረገው ድጎማም ካለፈው አመት ድጎማ የስድስት ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው ሲሉ አብራርተዋል::

ይህ እንግዲህ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው እንቅስቃሴ መንግሥት እያደረገ ያለው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠሉን ያመለክታል:: በየደረጃው ያለው አመራርና መላ አርሶአደር ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባ ሰፊ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት ይኖርበታል ብለዋል::

### የግብርና ሜካናይዜሽንና ኩታ ገጠም

በመኸር ላይ የሚታየው የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀም በበልጉም ይሠራበታል:: በሜካናይዜሽን የማረሱ፣ የማለስለሱ፣ የመዝራቱ፣ የመሰብሰቡ ሁኔታዎች ልክ እንደ መኸሩ ሁሉ በበልጉም በተጠናከረ መልኩ ይሠራበታል::

የኩታ ገጠም እርሻም በመኸሩ፣ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱም የሚሠራበት እንደመሆኑ በበልጉም ወቅት ይሠራበታል:: ሜካናይዜሽንን እያሰፋን ነው የምንሄደው:: ግብርናውን የማዘመን፣ ሜካናይዝድ የማድረግ እንቅስቃሴ በስፋት እየተሠራበት እንደመሆኑ በዚህም ላይ በትኩረት ይሠራል ሲሉም ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል:: በመኸርም፣ በበልግም በበጋ መስኖም ላይ በስፋት ይሠራበታል:: ሜካናይዜሽኑ እየጨመረ ነው የመጣው:: በቴክኖሎጂ በኩል የአርሶ አደሩም የባለሙያውም ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል:: መንግሥትም በተቻለው አቅም አርሶ አደሩ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን በቅርበት እየሠራ ነው ሲሉ አስታውቀዋል::

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የትምህርት ቤት ግብርና በረከቶች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የትምህርት ቤት እርሻዎች ወይም ግብርና ተግባራዊ የሆነ የትምህርት ልምድን ለተማሪዎች የሚሰጥ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይታመንበታል። ምክንያቱም እነዚህ ቦታዎች ትምህርታዊ ቦታዎች ቃለ ነቢብ ወደ ገቢር የሚቀየርባቸው ስፍራዎች በመሆን አገልግሎት ይሰጣሉ። እነዚህ እርሻዎች ብዙውን ጊዜ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ወይም አቅራቢያ እንዲኖሩ ተደርገው የሚፈጠሩ ስለሆኑም ለተማሪዎች የሚሰጡት ጥቅም ከዚህ መለስ የማይባል ሲሆን፤ አንዱም የመማር-ማስተማር ሥራውን መደገፍ እንደሆነ ታምኖበታል።

ተማሪዎች ስለ ምግብ ምርት እና ስለ ጤናማ አመጋገብ አስፈላጊውን እውቀት እንዲጨብጡ በማድረግ፣ ስለ እንስሳት ሕይወት እና ዑደቶች፤ እንዲሁም፣ ስለ ምግብ አመራረት ሂደቶች፣ ስለ ምርት መሰብሰብ፣ ማከማቻ እና ወደ ምግብነት መቀየርን እንዲማሩበት ዕድል በመስጠት፤ ስለ ተፈጥሮና አካባቢ እንክብካቤ፣ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅሞች፤ ኃላፊነት መውሰድን የመሳሰሉ ተግባራትን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። የግብርናው ዘርፍ ለአጠቃላይ ኅብረተሰቡና ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ያለውን ፋይዳ ይረዱ ዘንድ ያስችላቸዋል።

በትምህርት ቤት እርሻ ላይ የመሥራት ልምድ የቡድን ሥራን ለማዳበርም ሁነኛ መንገድ ነው። ለሌሎች ያለን አክብሮት፣ ኃላፊነት መውሰድና ለማኅበረሰቡ ቁርጠኝነትን ማሳየትም የሚቻልባቸው ቦታዎች ናቸው። በተጨማሪም ተማሪዎች ተግባራዊ ችሎታዎችን የሚያውቁባቸው የትምህርት ስፍራዎች ሲሆኑ፤ በተግባር ውስጥ ደግሞ ችግር መፍታትን፣ ውሳኔ መስጠትን፣ እቅድ ማውጣትንና የመሳሰሉትን ይማራሉ። በእነዚህ ልምዶችም ተማሪዎች ለግል እድገታቸው እና ለኅብረተሰቡ ደህንነት ፍቱን መድኃኒት ይሰጣሉ። ስለዚህም የእነዚህ ቦታዎች ዋና ግብ ለተማሪዎች የተግባር ልምድ መስጠት ነው።

የምግብ ምርት፣ ዘላቂ ግብርና እና ጤናማ አመጋገብ ደግሞ በእነዚህ ልምዶች የተማሪዎችን ግላዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ እድገትን የሚያመጣ አጠቃላይ ትምህርት ነውና ይህንን አውቀው እንዲራመዱ ያስችላቸዋል። ታዲያ እነዚህና መሰል ልምዶች በአገራችን ደረጃ እንዴት እየተተገበሩ ናቸው ከተባለ ለዛሬ ከተለመደው የገጠር ግብርና ወጣ ብለን የከተማውን፤ ከከተማም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያለውን እንቅስቃሴ እንመልከት። ይህም ሰፊ ስለሚሆን ወስነን በትምህርት ቤት ያለውን የከተማ ግብርና እናንሳ።

በ2014 ዓ.ም በ138 ትምህርት ቤቶች 147ሺህ 971 ነጥብ 38 ካሬ ቦታ ለማልማት ታቅዶ በ333 ትምህርት ቤቶች 279ሺህ 857 ካሬ ሜትር ማልማት ተችሏል። በዚህ ሥራ ላይ ደግሞ 5ሺህ 187 ሠራተኞች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ሆነዋል። በ254 ትምህርት ቤቶችም የኮምፖስት ማዘጋጀት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ ለጓሮ አትክልት ብቻ ሳይሆን ለመማር-ማስተማሩ ሥራም እጅጉን ጠቅሟል። እንደ አጠቃላይ በትምህርት ቤት ግብርናው 1ሚሊዮን 122ሺህ 180 ችግኞች የተተከሉ ሲሆን፤ አብዛኛው ወደ ምርትነት እንደተቀየረና ጥቅም ላይ እንደዋለ፤ በተፈጠረው የአመለካከት ለውጥም ሥራዎቹ እንደቀጠሉ የከተማ አስተዳደሩ የትምህርት ቢሮ መረጃ ያመላክታል።

የትምህርት ቤት ግብርናን እውን አድርገው እውቅናን ካገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል ደግሞ ገላን የወንዶች ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤትና ደጃዝማች ወንድይራድ አጸደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ይጠቀሳሉ።

ገላን ልዩ የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት መጀመሪያ ያየነው ሲሆን፤ በከተማ ግብርና በተደጋጋሚ ሽልማት አግኝቷል። ለዚህ ያበቃው ደግሞ የሥራ ድባቡን ከተማሪዎች እስከ መምህራን፤ ከጽዳትና ጥበቃ እስከ ጸሐፊና ርዕሰ መምህራን፤ ከምገባ ሠራተኞች እስከ የዶርም ተቆጣጣሪዎች ድረስ ለሁሉም የራሳቸው የሆነ የእርሻ ቦታ በመስጠት ወደ ተግባር ተገብቷል። በዚህ ደግሞ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ትምህርትም፣ ገንዘብም ማስገኘት ችሏል።

ትምህርት ቤቱ ከሁሉም በላይ በዚህ ሥራው ማህበረሰቡን ጭምር ማቅረብ ችሎበታል። ምክንያቱም በግቢው ውስጥ የተመረተውን ምርት ከሸያጭ ይልቅ በስጦታ መልክ ያቀርባል። በተለይም ርዕሳነ መምህራን የያዙት የእርሻ ስፍራ ብዙ አትክልትና ፍራፍሬዎችን የያዘ ሲሆን፤ ለተቸገረው የሚሰጥ፣ በአማረው ተቀጥፎ የሚበላ ነው። የሌሎቹ መምህራንም ቢሆን ይህንኑ መልክ የያዘ ነው።

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ደግሞ ከሌሎቹ ጭምር ወስደው ሸጠው ቤታቸውን እንዲደጉሙበት ይደረጋሉ። በመሆኑም ለምግብ ፍጆታቸው ከጓሯቸው ውጪ ብዙም አይገዙም። አብዛኛውን ፍጆታቸውን ከዚያው ይጠቀማሉ። ወጪያቸውንም ይቀንሳሉ። ይህንን ትምህርት ቤት ከሌላው ለየት የሚያደርገው ነገር የውሃ አጠቃቀሙ ሲሆን፤ ንጹህ ውሃን ሳይሆን ቆሻሻ ውሃን አጣርቶ በማቆር ነው ሥራ ላይ የሚያውለው። በዚህ ምክንያትም ከግቢ ውጪ የሚፈስ አንድ ጠብታ ውሃ የለም።

አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ እርሻዎች በርካታ ጠቀሜታዎች ያሏቸው ሲሆን፤ ዋነኛ አላማቸውም ጤናማ የአመጋገብ ልምዶችን ተማሪዎች እንዲያውቁ ማድረግ ነው። ተማሪዎች ስለ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ፣ ተገቢ የአፈር አያያዝን መማር ማስቻልም ነው። ይህ ልምድ ደግሞ ተማሪዎች ግላዊ እና ማህበራዊ እድገትን እንዲያመጡ ያስችላቸዋል። ጠቃሚ እሴቶችን እና ክሂሎትን እንዲያዳብሩም ይረዳቸዋል። የወደፊት ፍላጎታቸውንም ለመወሰን አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል።

በትምህርት ቤት እርሻዎች ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት እንደ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የሚወሰኑ ሲሆን፤ በገላን የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት ያለው የመልከአ ምድር ሁኔታ ለጥ ያለ ሜዳ ቢሆንም ብዙ ሥራን ግን የጠየቀ ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ስፍራዎች ድንጋያማና ቆሻሻ መድፊያ ነበሩ። ስለዚህም እነዚህን የእርሻ ቦታዎች ብዙ በመድከም ምርት ሰጪ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም ከቆሻሻ ማንሳትና ማጽዳት ባሻገር ድንጋያማውን ስፍራ ወደ ለም መሬት የመለወጡ ተግባራት በስፋት ተከናውኗል። ይህንን በማድረጋቸው ደግሞ ውጤታማ ለመሆን በቅተዋል። ከምድሩ በረከትም ማፈስ ችለዋል።

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ካሳሁን መርጋ እንዳሉን፤ ትምህርት ቤቱ ከችግኝ ጋር በተያያዘ ታሪካዊ ዳራ ያለው ነው። ምክንያቱም ታውቋቸው ሊሆን ይችላል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1997 ዓ.ም በቦታው ተገኝተው ችግኞችን ተክለዋል። በዚህም ዓመታትን ያስቆጠረ የግራር ዛፍ ምቹ ሆኗል። ግራር ካለ ደግሞ ቡና ግድ ነውና ትምህርት ቤቱ በቡና ተክል እንዲታወቅና ከዛፉ ፍሬ እንዲቀምስ ሆኗል። እንደ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች በአትክልትና ፍራፍሬም ተጠቃሚ ነው። ከዚህ ሻገር ሲልም ንብ የማነብ ተግባርን ያከናውናል።

የትምህርት ቤት ግብርና በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። አንዱ የመማር ማስተማር ሥራውን መደገፍ ነው። በዚህም ተማሪዎች ስለ እንስሳት የሕይወት ዑደት፣ ምርት መሰብሰብ እና ማቀናበር፤ በምርቶቹ ንግድ ውስጥ መሳተፍን ተማሪዎች እንዲያውቁ አስችሏል። ትምህርታቸውን አጠናቀው ቢወጡም እንዳይቸገሩ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም ኢንዱስትሪውን በእጅጉ የሚደግፈው እርሱ እንደሆነ በሚገባ ተረድተዋል። በትምህርት ውስጥ የሙያ አማራጮችን ለማየትም ችለውበታል ብለውናልም።

ግብርና ለምግብነት የሚውሉ ሰብሎችን እና የእንስሳት ምርምር እና ልማትን የሚያካትት ሳይንስ እንደሆነ ያነሱት ደግሞ የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ መስፍን መኩሪያ ናቸው። እሳቸው እንዳሉንም ሆነ በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው የግብርና ሳይንስ ባለሙያዎች በኅብረተሰባችን ውስጥ ያለውን የምግብ አቅርቦት ሳይቀር መፍትሄ ሰጥተዋል። በምገባ ሥርዓቱ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ብናነሳ እንኳን ሚናቸው የላቀ ነው። ለአብነት እንደ አገር 1ነጥብ5 ሚሊዮን ተማሪዎች በምገባ ፕሮግራም ውስጥ ተካተዋል። ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ደግሞ ከ700ሺህ በላይ ተማሪዎች በፕሮግራሙ ተካትተዋል። ይህንን የምገባ ፕሮግራም ለመሸፈን ደግሞ እጅግ አዳጋች ነው። ዋነኛው የገንዘብ ምንጫችን ደግሞ የዓለም ባንክ ነው። ይህንን ቢያቆም ተማሪዎችን ለመመገብ አስቸጋሪ ይሆናል። እናም ይህንን መተካት የሚቻለው በትምህርት ቤቶች ግብርናና ምርት ስለሆነ በስፋት ሊሠራበት ይገባል።

እንደ ትምህርት ቤት በከተማ ግብርና ብቻ ሳይሆን አዲስ በመጣው የሌማት ቱሩፋት ሳይቀር እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ለዚህ ማሳያው ደግሞ ንብ ማነብና አትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ በስፋት መሥራታችን ሲሆን፤ ዶሮ እርባታም የቅርብ ሥራችን ይሆናል። እስካሁን ባለው እንቅስቃሴ በቅንጅት ለመሥራት የመፈልፈያ ማሽን መግዛት ተችሏል። በቀጣይ ደግሞ የእንስሳት እርባታ የሚጀመር ይሆናል። ሁሉንም በማቀናጀት ተማሪዎቻችንን ጤናማ አድርገን ውጤታማ እንዲሆኑ እንሠራለን።

የትምህርት ቤት ግብርና የትምህርት ላብራቶሪ ነው። ምክንያቱም በሙከራና በእይታ ነገሮችን ማረጋገጥ ይቻልበታል። በተለይም የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ለሚማሩ ተማሪዎች መሠረት የሚሆን እውቀት የሚያስጨብጥ ነው። ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ቢሆን ቀጣይ የሕይወት ማረፊያቸውና መተዳደሪያቸውን የሚወስን ነው።



የገላን ልዩ የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት የከተማ ግብርና፣



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

የደጃዝማች ወንድይራድ ትምህርት ቤት የከተማ ግብርና በከፊል፣

ምክንያቱም ተማሪዎች የአትክልትና ፍራፍሬን አበቃቀል፤ ዓይነቶችን፤ የአፈር ዝግጅት፣ መትከል፣ ውሃ ማጠጣት፣ ማዳበሪያ፣ ተባዮችን እና በሽታን መቆጣጠር እንዴት እንደሚቻል ይማሩበታል። መሥራትን ልምድ ያደርጉበታልም ሲሉ ያብራራሉ።

ሌላኛው የተመለከትነው ትምህርት ቤት ደግሞ ደጅአዝማች ወንድይራድ የአጸደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ ልክ እንደ ገላን ሁሉ በትምህርት ቤት ግብርና የላቀ ተሸላሚ ነው። ትምህርት ቤቱ በቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት የብዙዎችን ሕይወት ሊታደግ የሚችል እና በከተማ እየተከናወነ ላለው የጓሮ አትክልት ልማት ሥራ ማዳበርያ ማቅረብ ያስቻለ በመሆኑ ተሸልሟል።

ይህ ት/ቤት ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት በመቀየርም የገቢ ማስገኛ ሥራን ያከናወነ ተቋም ነው። ይህ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል ተስማሚ እና መልሶ የመጠቀም አሠራርን ያመጣል። ለአረንጓዴና ጤናማ የከተማ ግንባታ ሂደትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። እናም ይህን በማድረጉ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ ሽልማት ተሸላሚ ሆኗል።

የዚህ ትምህርት ቤት የከተማ ግብርና ውጤት በአንድ በኩል ለተማሪዎች ምገባ ሲውል በሌላ በኩል ደግሞ በተለይም በዚህ በኑሮ ውድነት ወቅት ለማኅበረሰቡ አለኝታ መሆን ችሏል። እንዴት ከተባለ ምርቱን በቀላል ዋጋ በማቅረብ ችግር ፈቺነቱን አሳይቷል። ሌላውና ዋነኛ አላማው ደግሞ ተማሪዎች በግብርናው ዘርፍ በቂ እውቀት እንዲጨብጡ ማስቻሉ ነው። ለአብነት ተማሪዎች ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት መቀየር የሚችሉበትን እውቀት ቸሯቸዋል። ተፈጥሮን የሚያከም፤ ቆሻሻን ወደ ሀብትነት የሚቀይር አቅም እንዳላቸውም አሳይቷቸዋል።

ይህ ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን የአምስት ዓመት የከተማ ግብርና ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ሠርተው ነው። በዚህ እቅዳቸው የመጀመሪያው ዓመት የጓሮ አትክልት፤ በሚቀጥለው ዓመት ዶሮ፣ በሌሎቹ ዓመታት ደግሞ የዓሣ፣ ንብ ማነብና የእንስሳት ርባታን አካቶ ለመሥራት አስቦ ብዙዎቹን ተግብሯል። ቀጣይ ዓመት እቅዱም ዓሣውን ማስጀመር መሆኑን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ሰለሞን ክቤ ነግረውናል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ አሁን በተሠሩት ተግባራት ከራስ አልፎ ለአካባቢው ማህበረሰብ መድረስ ተችሏል። ሥራውን የሚያከናውነው ምርቶቹን በግቢው ውስጥ ባለው ሱቅ አርብ አርብ ለማህበረሰቡ በማቅረብ ሲሆን፤ በዚህም ትምህርት ቤቱ በወር በአማካኝ ከ18ሺህ ብር በላይ ገቢ እንዲያገኝ ሆኗል።

ትምህርት ቤቶች ግብርና ላይ መሥራታቸው በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የሚያነሱት ርዕሰ መምህሩ፤ በተለይም የከተማ ግብርና ለከተማ ልጆች እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዳሉ። ምክንያታቸው ደግሞ የከተማ ልጅ በቤቱ ብዙ ነገሮችን የማወቅ ዕድል የለውም የሚለው ነው። እንስሳትንና እጽዋትን ሳይቀር የማየት ዕድል ያለው በቴሌቪዥን መስኮት ብቻ ነው። ስለዚህም የትምህርት ቤት የእርሻ ቦታዎች ይህንን ችግራቸውን ከመፍታት አኳያ የማይተካ ሚና አላቸው። በተግባራዊ ልምምድም መፍትሄ ያገኙባቸዋል።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ከእርሻ እስከ አጨዳ እና አቀነባበር ድረስ ያለውን የግብርና ሂደት ይረዱበታል። ምግብ ከየት፣ እንዴት እንደሚመጣ እና ለማምረት ምን እንደሚያስፈልግ ይገነዘቡበታል። ጤናማ የአመጋገብ ልምዶችን ይቀስሙበታል። ማለትም ተማሪዎች ስለ ጤናማና የተመጣጠነ አመጋገብ አስፈላጊነት በትምህርት ቤት በንድፈ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም እያወቁ ይሄዱበታል። ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያጠናክሩበታልም። አካባቢያቸውን የመንከባከብ አስፈላጊነትንም ይረዱበታል።

ልጆች ከእፅዋትና ከእንስሳት ጋር በመገናኘት ስለ ብዝኃሕይወት አስፈላጊነት እና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ግንዛቤ ይይዙበታል። ሌላው የማህበራዊ ክሂሎት እድገትን ያመጡበታል። ማለትም በቡድን መሥራት ምን ያህል እንደሚጠቅም ያረጋግጡበታል። ችግር መፍታትንም ይማሩበታል። እነዚህ ማህበራዊ ክሂሎቶችን ማዳበር ከቻሉ ደግሞ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው እና በወደፊት ሥራዎቻቸው ላይ ትልቅ አቅም ይፈጥራሉ። እሴቶችን እና አዎንታዊ አመለካከቶችን ያዳብራሉም። ኃላፊነት መውሰድን ያውቃሉ። አወንታዊ እሴቶች እና አመለካከቶችን ከማዳበር አልፈው ለግላዊ እና ማህበራዊ እድገታቸው ይጠቀሙበታል ይላሉ።

አዎ፣ የትምህርት ቤት ግብርና ለተማሪዎች የትምህርት አቅም ማጎልበቻ ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ እረፍትም መስጪያ ስፍራ ነው። ምክንያቱም ቤተሰባቸው በኑሮ ውድነቱ እንዳይሰቃዩ ልምዱን በቤታቸው በማስፋት ተጠቃሚ ያደርጉበታል። ራሳቸውም ጤናማ የመማር-ማስተማር ሥራ ውስጥ እንዲገቡ ያስችላቸዋል። እናም ይህ አካዳሚያዊና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል በማለት ሀሳባችንን ቋጨን።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹መንግሥት ለሰላም መረጋገጥ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት የሚደነቁና የሚያስመሰግኑት ናቸው››

- አቶ ጋትሉዋክ ቡም

የጋምቤላ ነፃነት ግንባር ሊቀመንበር



አስቴር ኤልያስ

በአገር ደረጃ ሰላም ሰፍኖ ማየት የብዙዎች ፍላጎት ቢሆንም ጥቂት የማይባል አካል ግን ሰላምን ለማደፍረስ በብርቱ ሲጥር ይስተዋላል፡፡ ኢትዮጵያ አንዱን ችግር ታግዬ ጣልኩ ስትል ሌላ ተግዳሮት ደግሞ ከፊቷ ድቅን እያለ የልማት ሩጫዋን ለማስቀረት እግሯን ለመያዝ ይፈጨረጨራል፡፡ ይሁንና ታግላ እየጣለችና ድል እየተጎናጸፈች ዛሬ ላይ መድረስ ችላለች፡፡ እንዲያም ሆኖ በሙሉ አቅሟ ፊቷን ወደሰላም እንዳትመልስ የሚደረጉ ሴራዎች አሁንም እንዳሉ ይታወቃል፤ ያንንም ቢሆን በተለመደው ብርታቷና በዜጎቿ ጥረት ለማለፍ የተቻላትን ሁሉ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

ከዚህም አንዱ እምቢኝ! ብለው የያዙትን ዓላማ ከሰላማዊ ትግል ይልቅ ወደትጥቅ ትግል ወስደው ወደበረሃ ገብተው የሰነበቱ የተለያዩ ታጣቂ ኃይላት ጋር የተለያዩ ድርድሮችን በማካሄድ የሰላም እጇን መዘርጋት ተጠቃሽ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከሰሞኑ ከዓመታት በፊት ወደበረሃ ወርዶ ዓላማዬን በኃይል በመታገል አሳካለሁ ሲል ከነበረ የጋምቤላ ነጻነት ግንባር (ጋነግ) ጋር ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል፡፡ አዲስ ዘመንም ከዚህ ግንባር ሊቀመንበር ከሆኑት ከአቶ ጋትሉዋክ ቡም ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡

አቶ ጋትሉዋክ አንደኛ ዲግሪያቸውን ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል፡፡ በጋምቤላ ክልል የተለያዩ ቢሮዎች በኃላፊነት የሰሩ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ በክልሉ ከተማ ልማት ቢሮ በምክትል ቢሮ ኃላፊነት አገልግለዋል፡፡ በተመሳሳይ የክልሉ ባህልና ቱሪዝምን ቢሮ በምክትል ቢሮ ኃላፊነት መርተዋል፡፡ እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ እና በክልሉ ትምህርት ቢሮም በኃላፊነት ደረጃ አገልግለዋል፡፡

የክልሉ መምህራን ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአስተዳደር ዲን ሆነም ሰርተዋል፡፡ ከእነዚህ የኃላፊነት ስራ በኋላ ከአመራር እርከን ወርደው በባለሙያ ደረጃ ተመድበው እየሰሩ የነበሩና ከዚያም ነፍጥ አንግበው ለመታገል ወደበረሃ የወረዱ ሲሆኑ በአሁኑ ወቅትም መንግሥት የሰጠውን ዕድል ተጠቅመው በሰላማዊ መንገድ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ ከእኚህ ከወቅታዊ እንግዳችን ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ ሰላምን የሚገልጹት እንዴት ነው? ፋይዳውስ ምንድን ነው ከሚለው ጥያቄ ቃለ ምልልሳችንን እንጀምር?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** እኔ ሰላምን የምተረጉመው ማንኛውም ዜጋ በሰላም ወጥቶ በሰላም ወደቤቱ መመለስ ሲችል ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት እኩል መብት ሲኖረው እና ይህ መብት ደግሞ በአግባቡ ሲጠበቅለት ነው ፡፡ ጉዳዮቻችን በሕግ እና በሕግ ብቻ ሲታዩ ማለት ነው ፡፡ አንዱ የበላይ ሌላው ደግሞ የበታች የሚሆን ከሆነ ግን ሰላም ያለ የሚመስለው ለጊዜው እንጂ ዘለቄታ አይኖረውም፡፡

የትኛውም ሰው በቀላሉ እንደሚረዳው ሰላም እንዳይኖር የሚያደርጉ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋንኞቹ ናቸው ብዬ ከምጠቅሳቸው አንዱ የምለው የሰው ልጅ እኩልነት ሳይረጋገጥ ሲቀር ነው፡፡ ሌላው ደግሞ መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎት ሳይሟላ ሲቀር ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የመልካም አስተዳደር ችግር የሚፈጠር ከሆነም ሰላም ምኞት ብቻ ሆኖ ሊቀር ይችላል፡፡

ሰላም የማይኖር ከሆነ አገር የምታጣው ብዙ ነገር አለ፡፡ በተለይም የአገር ኢኮኖሚ ከማደግ ይልቅ ማሽቆልቆል ይጀምራል፤ ከዚህ በተጨማሪ አምራች የሆኑ ዜጎችን አገር ለማጣት ትገደዳለች፡፡ ይህ ሲሆን ቀደም ሲልም የነበራት ገጽታም የምታጣ ትሆናለች፡፡ ይህ እንዳይሆን ደግሞ መንግሥት ለሰላም መስፈን ሲል እያከናወናቸው ያሉ እንቅስቃሴዎች መልካም የሚባል ነው፡፡ ይህ አካሄዱም የሚያስደንቀው እና የሚያስመሰግነውም ጭምር ነው፡፡ ይህን መልካም ስራ በቀጣይም እንዳይደፈርስ በማድረግ አጠናክሮ የሚያስቀጥል ከሆነ የያዘውን ግብ ከዳር ያደርሳል የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከሰሞኑ ሰላማዊ ትግሉን ለመቀላቀል ጥሪ ተቀብላችሁ መጥታችኋል፤ እርስዎ ይመሩት የነበረው ድርጅት ዋና ዓላማው ምን ነበር?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** የድርጅታችን ዋና ዓላማ የነበረው የበለጸገ ማኅበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ በተለይም የራሱን መብት በራሱ መወሰን የሚችል ማኅበረሰብ ለመፍጠር ነበር የትጥቅ ትግል ውስጥ የገባነው፡፡ በተለይም የጋምቤላ ሕዝብን ከጭቆና እና ከረሃብ ጎዳና ማስወጣት ዋናው ዓላማ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ እኩልነትን ለማረጋገጥም ሲባል ነበር ወደበረሃ ለመውረድ የተንደረደርነው፡፡

ወደ በረሃ ከመሄዳችን በፊት በዚያው በጋምቤላ ውስጥ ሆነን ለመታገል ሞክረን ነበር፡፡ ይሁንና እንዳሰበነው ሊሆንልን አልቻለም፡፡ በዚህ የተነሳ ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ እና አስገዳጅም ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ምርጫችን ወደ በረሃ በመውረድ መታገል ነበር፡፡

በዚህ ውስጥ እያለን በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሰላም ጥሪ ተደረገልን፡፡ በተደረገልን ጥሪ መሰረትም መልሰን እንደድርጅት መነጋገር እና መወያየት ጀምርን፡፡ ከተወያየንም በኋላ ለሰላም ያለንን ቁርጠኛነት ለማሳየት ተዘጋጀን፡፡

የሰላም ቁርጠኝነታችን ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረ ሲሆን፣ ይህንን የሰላም ፈላጊነታችንን እናረጋግጥላቸው በሚል ወስነን ወደ ሰላማዊ ትግል ፊታችንን ለማዞር ተስማማን፡፡ ለዚህም ነው የበረሃ ትግልን ወደጎን በማድረግ ሰላማዊ የሆነ ትግል ለመታገል የመጣነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንደጠቀሱት የድርጅቱ ዓላማ የበለጸገ ማኅበረሰብ መፍጠር እና በተለይም የጋምቤላን ሕዝብ ከጭቆና ጎዳና ማስወጣት ነው፤ በዚህ ዓላማ ለምን ያህል ጊዜ ታገላችሁ? ያገኛችሁትስ ውጤት ምን ነበር?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** የውስጥ ትግል በመተው ወደበረሃ ወርደን የቆየነው ለሁለት ዓመት ያህል ነው፡፡ በነበርንበት የትጥቅ ትግል ውስጥ ሆነን ማንኛውም በትጥቅ ትግል ውስጥ ያለ ድርጅት ሊያጋጥመው የሚችለው ችግር ገጥሞናል ከዚህም ውስጥ ወደ በረሃ አብረውን የወረዱ የምንወዳቸው የትግል አጋሮቻችንን በሞት አጥተናል፡፡

በሞት ያጣናቸው ጓዶቻችን ከጎናችን ባለመኖራቸው የሚያስቆጭ ነው፡፡ በትጥቅ ትግል ወቅት የአካል ጉዳት የደረሰባቸውም ጓዶቻችን አሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የደረሰብን ብዙ እንግልትም አለ፡፡

በእርግጥ የጓዶቻችንን ከአጠገባችን ማጣት ቁጭታችንን ከፍ ያደረገው ነው፡፡ ይሁንና የሕዝብ ጥያቄ ያለመሳሪያ ድምጽ መመለስ የሚቻል ከሆነ ስለምን መስዋዕትነት እንከፍላለን ወደሚለው አመለካከት መምጣት ችለናል፡፡ ይህ ደግሞ መሆን አለበት ብለን የምናምንበት አመለካከት ነውና ወደዚህ ጉዳይ መምጣት ችለናል፡፡ ምክንያቱም የያዝነው የሕዝብ ጥያቄ መሰረታዊ እና ሕገ መንግሥታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄዎች እስከሆኑ ድረስ መመለስም ያለባቸው በሰላማዊ መንገድ ብቻነው ብለን እናምናለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በወቅቱ ሕገ መንግሥታዊ ናቸው ያሏቸው ጥያቄዎች የትኞቹ ነበሩ?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** ሕገ መንግሥታዊ መሰረት ያላቸው ጥያቄዎች ናቸው ካልናቸው መካከል አንዱ የእኩልነት ጥያቄ ነው፡፡ ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል ውስጥ የሚገኙ ነባር ብሔረሰቦች በእኩል እየተዳኙ እና መሰረታዊ አገልግሎት ብሎም የፖለቲካ እኩል ተጠቃሚ ናቸው ማለት አንችልም ነበር፡፡ በዚህ የእኩል ተጠቃሚነት ላይ ችግር አለ፡፡ ለምሳሌ ከስልጣን ብሎም ከሀብት ክፍፍል ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችል ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም ችግር አለ፡፡

እውነቱን ለመናገር በብልጽግና ጊዜ እንደ አገር የተጀመሩ በጣም በርካታ ጠንካራ ስራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ጠንካራ የምንላቸው ስራዎች ልክ እንደሌላው ክልል ሁሉ በጋምቤላ ክልል ውስጥ መታየት መቻል አለባቸው ባይ ነን፡፡ ለምሳሌ እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት እየተከተልን ያለው ስርዓት የኅብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝምን ስርዓት ነው፡፡ ይህን የኅብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝምን ስርዓት እስከተከተልን ድረስ በጋምቤላም ክልል መሆን ያለበት በዚሁ መሰረት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ስለዚህ የመጀመሪያው ክልሉም መመራት ያለበት በብዙኃን ነው ባይ ነኝ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያለውም የብሔር ውክልና እስከሆነ ድረስ ያንኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስሌቱ በሬሽዮ የሚሰራ ሲሆን፣ ለምሳሌ ከኦሮሚያ፣ ከአማራ እንዲሁም ከሶማሌ እና ከሌሎችም እንደሆነው ሁሉ ጋምቤላ ላይም ተግባራዊ መደረግ አለበት እንላለን፡፡

**‹‹መንግሥት ለሰላም መስፈን ሲል እያከናወናቸው ያለው እንቅስቃሴ መልካም የሚባል ነው፡፡ ይህ አካሄዱም የሚያስደንቀው እና የሚያስመሰግነውም ጭምር ነው፡፡ ይህን መልካም ስራ በቀጣይም እንዳይደፈርስ በማድረግ አጠናክሮ የሚያስቀጥል ከሆነ የያዘውን ግብ ከዳር ያደርሳል የሚል እምነት አለኝ››**

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ‹‹መንግሥት ለሰላም መረጋገጥ...

ከገጽ 10 የዞረ

ጋምቤላ ክልል ላይ ለምሳሌ የኑዌር ብሔረሰብ በሕዝብ ብዛት ስሌት ሲታይ ከጋምቤላ ክልል 47 በመቶ ያህል ነው:: በተመሳሳይ ስሌት ሲታይ የአኙዋክ ብሔረሰብ ደግሞ 21 በመቶ ነው:: ማጀንግ ደግሞ አራት በመቶ ሲሆን፣ ኮሞ እና ኦፖ 08 በመቶ ነው:: ሌሎች የተቀሩት ደግሞ ከመሃል ኢትዮጵያ የመጡ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የሆኑ ኢትዮጵያውያን ብሔር እና ብሔረሰቦች ናቸው:: ስለዚህ ይህን መሰረት በማድረግ በክልሉ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ይሁን የውክልና አሰጣጥ ይስተካከል የሚል አቋም ነው ያለን::

ምክንያቱም ከማዕከላዊ መንግሥት አሰራር የምንለይበት ምንም ዓይነት ምክንያት የሚኖር አይመስለኝም:: እየተዳደርን ያለነው በአንድ መንግሥት ነው:: ከዚህ ውጪ መሔድ እንደሌለብንም ስለምናምን ሕገ መንግሥቱ ተግባራዊ ይደረግ ነው እያልን ያለው::

ካለፈው ምርጫ ጋር በተያያዘም ቅሬታ ነበረን፤ በምርጫው እኔም እንደ አንድ ግለሰብ ተወዳድሬያለሁ:: በወቅቱ እኔ ስወዳደር የነበረው የጋምቤላ ነጻነት ግንባርን ወክዬ ሳይሆን በሌላ ድርጅት ውክልና ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የሰላም ትግሉን እንድትቀላቀሉ ጥሪ ደርሷችሁ አምናችሁበት ከመጣችሁ በኋላ የተስማማችሁበት ጉዳይ ይኖር ይሆን?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** አዎ! የተስማማንባቸው ጉዳዮች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ቀደም ሲል የነበርንበት ይታወቃል፤ ስናካሄድ የነበረውም የትጥቅ ትግል እንጂ የሰላም ትግል አልነበረም:: ስለዚህም የደረሰንን ጥሪ ተቀብለን በሰላም ለመታገል ስምምነታችንን በፊርማችን አረጋግጠናል:: በአሁኑ ወቅት ቀደም ሲል በጋምቤላ ነጻነት ግንባር ስም ላለፉት ጊዜያት ሲታገል የነበረ ኃይል ከዚህ በኋላ በኃይል ታጥቆ የሚታገል አይሆንም::

ሰላምን የምንፈለግ በመሆናችን የሰላም ትግሉን በይፋ ተቀላቅለናል ማለት ነው:: ይህ በራሱ ራሱን የቻለ ዋና ስምምነት ነው ባይ ነኝ:: በሌላ በኩል ደግሞ የታጠቁ አባላቶቻችን የትጥቅ መሣሪያቸውን መፍታት ብቻ ሳይሆን ወደ ስልጠናም እንዲገቡ ተደርጓል:: ከዚህ በተጨማሪ በእስር ቤት የነበሩ የእኛ አባላት ከእስር እንዲፈቱም ላቀረብነው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ እንደሚሰጡን ተስማምተናል:: በዚህ ጉዳይም ሕገ መንግሥቱን መሰረት ያደረገ ፊርማ ተፈራርመናል:: በተለይ ደግሞ ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ እንደሚሰጥም ነው ተስማምተን የተፈራረምነው::

**አዲስ ዘመን፡-በማረሚያ የሚገኙ አባላቶቻችሁ ምን ያህል ናቸው? ምን ያህሉ ታራሚስ ነው እንዲፈታ ከስምምነት የደረሳችሁት?**


**አቶ ጋትሉዋክ፡-** እንዲፈቱልን ከስምምነት ላይ የደረስነው 15 አባላት ናቸው:: ከዚህ በፊት በፌዴራል ደረጃ የታሰሩ አባላት ነበሩ:: ነገር ግን እነርሱ ተፈትተዋል::

**አዲስ ዘመን፡- የትጥቅ ትግሉን በመተው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማካሔድ ወስናችኋልና ከክልሉ መንግሥት ጋር በምን ዓይነት ሁኔታ ለመጓዝ ነው ያቀዳችሁት?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** የሰላም መንገድ ለመከተል እስከመጣን ድረስ ከክልሉ መንግሥት ጋር ለመስራት ያሰብነው ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ነው:: በተለይም በምንጋራቸው ጉዳዮች ላይ መስራት የሚጠበቅብን በጋራ እና በአንድነት ነው ብዬ አስባለሁ:: ምክንያቱም ከሰላም ብዙ ማትረፍ ይቻላል በሚል መንፈስ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማካሔድ እስከተስማማን ድረስ የክልሉ የሰላም ጉዳይ ይመለከተናል:: ክልሉ ሰላም ሆነ ማለት የሁላችንም ሰላም ተጠበቀ እንደማለት ነው:: ክልሉ ሰላም ሆነ ማለት ልማቱም እድገቱም ይመጣል:: ለዚህ ደግሞ በአብሮነት መስራቱ ተገቢ ይመስለኛል::

ሌላው ቀርቶ የሚነሱ የእኩልነትም ሆኑ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ቢኖሩ በጋራ በመስራት የተሻለ እድገት በማስመዝገብ መመለስ የሚቻል ሲሆን ይህም ስራ የጋራ ስራ ይሆናል የሚል አተያይ አለኝ:: ምክንያቱም የእኛ ፍላጎት ከክልሉ ጋር በኅብረት መስራት ነው:: ይህ

**«ሰላም በሌለበት የማንንም መብት ለማክበር ያስችግራል:: ጥያቄ ለማስመለስም ሆነ በጋራ ለመልማት የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው:: የሕዝብ ጥያቄን መመለስም የሚቻለው ሰላም ሲረጋገጥ ነው»**



ግን በቀጣይ በጋራ የምናየው ጉዳይ ይሆናል ብዬ አስባለሁ እንጂ አሁን ላይ ሆኜ እርግጠኛ መሆን እና መገመት አልችልም::

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንዴ በጋምቤላ ክልል በኩል ኢትዮጵያ የምትዋሰንበት ድንበር አካባቢ የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ፤ በዚህ ጉዳይ ያልዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** በእርግጥ ይህ ራሱ የጋራ ስራ ነው እንጂ የክልሉ መንግሥት ስራ ብቻ አይደለም የሚል እምነት አለኝ:: ደግሞም የፌዴራል መንግሥትም ስራ ነው:: በተለይ ደግሞ በጋምቤላ ክልል በኩል ከደቡብ ሱዳን ጋር የምንጋራው ድንበር ስላለ አንዳንድ ችግሮች ሲከሰቱ ይስተዋሉ ነበር:: በእርግጥ ችግሩ ወደከፋ ደረጃ ከመዝለቁ በፊት መንግሥት ከክልሉ ጋር በመሆን መፍትሔ ያለውን እያስቀመጠና እየሰራ እዚህ መድረስ ተችሏል::

እንደሚታወቀው ደግሞ ከደቡብ ሱዳን ወደ ጋምቤላ ክልል የሚገቡ የሙርሌ ጎሳዎች አሉ:: ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ የሚያመላልስ ቡድንም አለ:: ይህ በተለይ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርን መከላከል በዋናነት የፌዴራል መንግሥት ስራ ነው:: ከዚህ ጎን ለጎን የክልሉ መንግሥት ብሎም እኛም አጋር ሆነን የአገራችንን እንዲሁም የክልላችንን ሰላም የማስጠበቅ ኃላፊነት እንዳለብን እረዳለሁ:: በዚህ አጋጣሚ እንዲያውም እኛ በጋራ ለመስራት ቆርጠን ተነስተናል፤ ይህ የሚሆነው ግን የክልሉ መንግሥት ዕድል ሲሰጠን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ የትጥቅ ትግሉን ትታችሁ ወደ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል መጥታችኋል፤ ከዚህ በኋላ ክልሉም አገርም ሰላም እንዲሆን ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** ከዚህ በኋላ ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ መሰረታዊ የሆኑ የሕዝብ ጥያቄዎች በአግባቡ ምላሽ ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ነው:: እንደ እኔ እምነት መሰረታዊ የሆኑ የሙብት ጥያቄዎች ወይም የአንድ ማኅበረሰብ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት የሌላውን ማኅበረሰብ የማይጎዳ እስከሆነ ድረስ ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ያን ያህል የሚከብድ ነው ብዬ አላስብም:: እናም መሰረታዊ የሆኑ የሕዝብ ጥያቄዎች ብሎም ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄዎች መፍትሔ ማግኘት አለባቸው::

እነዚህ ጥያቄዎች በማይመለሱበት ሁኔታ ብዙ ሰላም አለ ማለት አያስደፍርም:: ጥያቄዎች በሰለማዊ መንገድ ባልተመለሱበት ቦታ ሰላም መጣ ቢባል የተቀበረ ፈንጂ ይሆናል እንጂ ትክክለኛ ሰላም ነው ለማለት ያስቸግራል::

ስለዚህ መሆን ያለበት ነገር ቢኖር መሰረታዊ የሆኑ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆን፣ ይህም ማለት የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም ማለት ነው:: ይህ ሲሆን በአገር ደረጃም ሆነ በክልል ደረጃ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ከፍ ያለ ሚና ይኖረዋል::

ለምሳሌ የእኛን ድርጅት መውሰድ ትችያለሽ፤ እኛ በተደረገልን የሰላም ጥሪ አገር ውስጥ ገብተናል:: ይሁንና አንግበን የነበሩ ጥያቄዎች ገና አልተመለሱም:: ቢሆንም የእኛ አመለካከት በመጀመሪያ ለሰላም ቅድሚያ እንስጥ የሚል ነው:: ምክንያቱም ሰላም ከሁሉ መቅደም ያለበት ጉዳይ ነው:: ሰላም በሌለበት የማንንም መብት ለማክበር ያስቸግራል:: ጥያቄ ለማስመለስም ሆነ በጋራ ለመልማት የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው:: የሕዝብ ጥያቄን መመለስም የሚቻለው ሰላም ሲረጋገጥ ነው:: ይህ ሰላም የሚመጣው ደግሞ በአንድ አካል ብቻ በሚደረግ ጥረት ሳይሆን በጋራ ነው:: እኛም ይህን በመገንዘብ የሰላሙ አካል ለመሆን ፈቅደን ነው ወደ አገራችን የገባነው::

**አዲስ ዘመን፡- የተረጋጋች አገርን ከመመስረት አኳያ የእናንተ ድርሻ ምን ይሆናል?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** የእኛ ድርሻ የሚሆነው የተመኘነው ሰላም ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ ከመንግሥት ጎን በመሆን በጋራ መስራት ነው:: እንደ አንድ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ብሎም ለሰላም እንደሚተጋ ድርጅት የበኩላችንን ለሰላም መደረግ ያለበትን ስራ ሁሉ እንሰራለን ብዬ አምናለሁ:: በሌላ በኩል እንደ ዜጋ ሲታይ ለሰላም የተቻለኝን ሁሉ ለማበርከት ግዴታ እንዳለብኝ ይሰማኛል:: ስለዚህም በአገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለብን:: ለዚህ ነው ስለሰላም ሲባል ከመንግሥት ጎን በመሆን እንሰራለን የሚል አቋም የያዝነው::

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት እንደ አገር የያዛቸው ትልልቅ አጀንዳዎች አሉት፤ ከዚህ አኳያ ለተፈጻሚነታቸው የእናንተ ሚና ምንድን ነው?**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** የእኛ አስተዋጽኦ የሚሆነው በመንግሥት የተያዙ ትልልቅ አጀንዳዎች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው አቅማችን በፈቀደው ሁሉ በጋራ መስራት ነው:: ልማቱ ለአገራችን የሚደረግ ስራ እስከሆነ ድረስ እኛም የዚሁ ተጠቃሚዎች ነንና የቻልነውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁዎች ነን::

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን መረጃ ከልብ ላመሰግንዎ እወዳለሁ::**

**አቶ ጋትሉዋክ፡-** እኔም ዕድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ::

# ዓለም አቀፍ

## የሱዳን ቀውስ ከሶሪያ እና ከሊቢያ ሊከፋ እንደሚችል የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አስጠነቀቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የቀድሞው የሱዳን ጠቅላይ ሚኒስትር አብዳላ ሐምዶክ በአገራቸው የተከሰተው ግጭት ከሶሪያ እና ከሊቢያ የከፋ ሊሆን እንደሚችል አስጠነቀቁ። ውጊያው የሚቀጥል ከሆነም "ዓለምን የሚያስጨንቅ ቅዠት" ሊሆን ይችላል ብለዋል አብደላ ሐምዶክ።

በተፋላሚዎቹ ጄኔራሎች መካከል እንዲራዘም ከስምምነት የተደረሰው የተኩስ አቁም በዋና ከተማዋ ካርቱም ውስጥ በተፈጸሙ የአየር ጥቃቶች እየተጣሰ መሆኑ ተነግሯል።

ሁለት ሳምንት የሆነው ውጊያ እስካሁን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈ ሲሆን፣ አስር ሺዎችን ደግሞ ከአገራቸው እንዲሰደዱ አድርጓል።

ለሦስት ቀናት የቆየው የተኩስ አቁም ሐሙስ ዕለት ለተጨማሪ ቀናት እንዲራዘም የተደረገው በሱዳን ጎረቤት ሀገራት እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት፣ በአሜሪካ እና በዩናይትድ ኪንግደም ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ነው።

ነገር ግን ለ72 ሰዓታት የተራዘመው የተኩስ አቁም እየተከበረ እንዳልሆነ ሪፖርቶች እያመለከቱ ነው። በአንዳንድ የካርቱም አካባቢዎች የአየር፣ የታንክ እና የመድፍ ጥቃቶች ቀጥለዋል ተብሏል።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሐምዶክ በኬንያ ዋና ከተማ በተካሄደ ጉባኤ ላይ ሁለቱን ተቀናቃኝ ጄኔራሎች ወደ ሰላም ንግግር ለማምጣት የተባበረ ዓለም አቀፍ ጥረት እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

"ሱዳን የተለያዩ ሕዝቦች ያሉባት ግዙፍ አገር ናት... ግጭቱ ዓለምን እንቅልፍ የሚነሳ ቅዠት ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ" ሲሉም ተናግረዋል ሐምዶክ።

"ይህ በሀገሪቱ ሠራዊት እና በትንሽ አማጺ ቡድን መካከል የሚካሄድ ጦርነት አይደለም። በደንብ በሰለጠኑ እና በታጠቁ ሁለት ሠራዊቶች መካከል የሚካሄድ አይነት ጦርነት ነው" ብለዋል።

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሱዳናውያን ከጦርነቱ ለመሸሽ ወደ ጉረቤት ሀገራት እየተሰደዱ ነው፡፡

አሁን ውጊያ በገጠሙት ጄኔራሎች በመፈንቅለ መንግሥት ከሥልጣን ከመወገዳቸው በፊት ለሁለት ዓመት ያህል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው አገሪቱን የመሩት አብደላ ሐምዶክ፣ በሱዳን የተከሰተው ቀውስ በሶሪያ እና በሊቢያ ካጋጠመው የእርስ በርስ ጦርነት የከፋ ሊሆን እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።

ለዓመታት በሶሪያ እና በሊቢያ በተካሄዱት ደም አፋሳሽ ጦርነቶች በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ ሚሊዮኖች ደግሞ ለስደት ተዳርገዋል። በተጨማሪም በዙሪያቸው ባሉ ሀገራት ውስጥም አለመረጋጋትን አስከትለዋል።

በሀገሪቱ ሠራዊት እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች መካከል የተፈጠረውን የሥልጣን ፉክክር ተከትሎ ነበር ወታደራዊ ግጭቱ ሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓ.ም. የተቀሰቀሰው።

አሁን ለተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያቱ አገሪቱ ወደ ሲቪል አስተዳደር በምትመለስበት እና አንድ መቶ ሺህ የሚሆኑት የሰለጠኑ አባላት ያሉት የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ወደ አገሪቱ ሠራዊት በሚካተትበት ዕቅድ ላይ በሁለቱ ጄኔራሎች መካከል አለመግባባት መፈጠሩ ነው።

ከ20 ዓመት በፊት ዳርፉር ውስጥ ከተፈጸሙ የጦር ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ደጋፊዎቻቸው በዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ተፈላጊ በመሆናቸው ሁለቱም ጄኔራሎች በሱዳን መንግሥት ውስጥ ያላቸውን ሥልጣን ማጣት በእጅጉ ያስፈራቸዋል።

በውጊያው ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የካርቱም ነዋሪዎች በምግብ፣ በውሃ እና በነዳጅ ችግር እየተሰቃዩ ይገኛሉ።



ከዋና ከተማዋ ባሻገር በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች ግጭቶች እየተካሄዱ ሲሆን፣ በተለይ በዳርፉር ውስጥ የሚሊሻ ቡድኖች የገበያ ስፍራዎችን በመዝረፍ በእሳት ማጋየታቸው ተዘግቧል።

የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መሪ ጄኔራል ሔሜቲ የተኩስ አቁሙ ከተራዘመ በኋላ በተዋጊዎቻቸው ላይ "ያልተቋረጠ" ጥቃት እየተካሄደ መሆኑን በመጥቀስ፣ ጦርነቱ እስካላበቃ ድረስ ድርድር እንደማይኖር ለቢቢሲ ተናግረዋል።

"ሱዳንን ማውደም አንፈልግም" ያሉት ሔሜቲ፣ ለጦርነቱ ተቀናቃኛቸውን የሠራዊቱን ጄኔራል አብደል ፈታህ አል ቡርሐንን ተጠያቂ አድርገዋል።

ጄኔራል አልቡርሐን በጊዜያዊነት ደቡብ ሱዳን ውስጥ ከሔሜቲ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ለመነጋገር ፈቃደኛ መሆናቸውን መግለጻቸው ይታወቃል።

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሱዳናውያን ባገኙት የመጓጓዣ ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ከጦርነቱ ለመሸሽ ኢትዮጵያን ጨምሮ ወደ ሱዳን ጉረቤት ሀገራት እየተሰደዱ ነው።

ከሱዳናውያን በተጨማሪ የተለያዩ ሀገራት የተራዘመውን የተኩስ አቁም ጊዜ በመጠቀም ዜጎቻቸውን በየብስ፣ በባሕር እና በአየር ከአገሪቱ ለማስወጣት ጥረት እያደረጉ ነው ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።


## Invitation to Bid

Invitation to BC Category V or GC Category V or above Contractors for the Construction of the first phase /up to first floor slab/ of Shewarobit town water supply and sewerage service office G+4 mixed use building

**Procurement Reference Number...SHWSSO/NCB-01/01-2023**

1. Shewarobit Town water supply and sewerage service office invites the bid for the Construction of the first phase /up to first floor slab/ of G+4 mixed use building through National Competitive Bidding (NCB) Procedures.
2. Shewarobit Town Water Supply and Sewerage Service office invites sealed bids for BC Category V or GC Category V or above Contractors that have Trade License valid for the current Ethiopian Fiscal Year (2015), VAT Registration Certificate, TIN Certificate, valid Tax Clearance Certificate, Registration in the supplier list of Public Procurement and Property Administration Agency.
3. Bidding will be conducted in accordance with the OPEN Bid Tendering Procedures Contained in the Public Procurement Proclamation of the Federal Government of Ethiopia.
4. A complete set of Bidding Documents prepared in English may be purchased by interested eligible bidders from Shewarobit Town water supply and sewerage service office Procurement and Finance team, from 8:30am up to 5:00 pm in working days, and upon payment of a non-refundable fee of Br 1000.00 (One thousand Birr only), starting from the first date of this announcement published on the newspaper for the consecutive 21days.
5. Interested eligible bidders may obtain further information and clarification on the bid documents from Shewarobit Town water supply and sewerage service office.
**Address Ethiopia, Shewarobit, 03 kebele, around Shewarobit town administration, in front of Bisrat College; Tel. +251-33-664-00-40**
6. Bid proposals comprising One Original and Two Copies of the separately sealed Technical (Qualification) and financial Proposals should be presented to the address mentioned above on the 21st day from the first date of this announcement published on the newspaper at 10:00 am (4:00 Local time morning) as it clearly mentioned on the tender document, and will be opened on the same date at 10:30 am (4:30 Local time morning). Late bids shall be rejected and will be return unopened to the Bidder.
7. The bids must be accompanied by a Bid security of 250,000.00 birr (Two hundred and fifty thousand), as specified in the tender documents and separately sealed within the technical document. The Bid security shall only be in the form of Cash or Certified Cheque payable Order (CPO).
8. Bids will be opened in the presence of the Bidders' representatives
9. Shewarobit town water supply and sewerage service office Employer reserves the right to accept or reject any or all bids
10. Note: We inform you that Saturday is a working day until 5:00 p.m.

**Tel-+251336640040**
**SHEWAROBIT,ETHIOPIA**
**AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE, NORTH SHOA**
**SHEWAROBIT TOWN**
**WATER SUPPLY AND SEWARAGE SERVICE OFFICE**



## በድጋሚ የወጣ የከባድ ተሽከርካሪዎች ባትሪ
## የአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ

### የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር RE-ESLSE/KLT/05/2015


በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ የብስ ትራንስፖርት ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት በ2015 በጀት አመት የከባድ ተሽከርካሪዎችን ባትሪ ብቃት ካላቸው የአገር ውስጥ አቅራቢዎች በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

1. በዚህ ጨረታ ተካፋይ የሚሆኑ ተጫራቾች
1.1 የዘመኑ ግብር የተገበረበት ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ
1.2 የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ
1.3 የግብር ከፋይነት /Tin Number/ ምዝገባ ሰርተፊኬት ማቅረብ አለባቸው፡፡
1.4 በመንግስት ንብረት ማስወገድ እና ግዥ ኤጀንሲ የተመዘገቡበትን ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ዘወትር በሥራ ሰዓት ከቅ/ጽ/ቤቱ ግዥ ዋና ክፍል ቢሮ ቁጥር 108 ቀርበው የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid Bond) 100,000.00 ብር (አንድ መቶ ሺ ብር) በባንክ በተመሰከረለት ቼክ (CPO) ብቻ Ethiopian Shipping & Logistics Service Enterprise Kality Branch Office የሚል በማሠራት ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የነጠላ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋ የተ.እ.ታ ያካተተ መሆኑ መገለፅ አለበት፡፡
5. ተጫራቾች ጨረታው ለመጀመሪያ ጊዜ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 21 ተከታታይ ቀናት እና ጨረታው እስከሚከፈትበት እለት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይችላሉ፡፡
5.1 የሚያቀርቡትን የጨረታ ቴክኒካል ሰነድ ኦሪጅናል እና ኮፒ እንዲሁም የፋይናንሻል ሰነድ ኦሪጅናል እና ኮፒ በመለየት በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግና በታሸገው ኤንቨሎፕ ላይ የጨረታ ቁጥር RE- ESLSE/KLT/05/2015 በመፃፍ ቅ/ጽ/ቤቱ የግዥ ዋና ክፍል ቢሮ ቁጥር 108 በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት አለባቸው፡፡
6. ጨረታው 22ኛው ቀን /በዓል ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን/ ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ እለት 4፡30 ሰዓት በቅ/ጽ/ቤት የስብሰባ አዳራሽ ቢሮ ቁጥር 102 ተጫራቾች/ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊነት ደብዳቤ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ውል ማሰር ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. ቅ/ጽ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር** 0114-40-14-98 / 0114-40-40-78

**የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

# ስፖርት



## ትኩረት ያልተሰጠው የጠረጴዛ ቴኒስ



ዓስማየሁ ግዛው

እንደ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ያላደጉ ከሚመስሉና ብዙዎች ውጤታማነታቸውን ካልተረዷቸው ስፖርቶች መካከል ጠረጴዛ ቴኒስ አንዱ ነው:: በዚህ ስፖርት ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ጥሩ እንቅስቃሴ አላት:: ባለፈው ዓመት በተካሄደው የቀጣናው ውድድርም በሴቶች ብሔራዊ ቡድን ዋንጫ መገኘቱ ማሳያ ነው:: ይሁንና ስፖርቱን ይበልጥ ውጤታማና አገርም በትልልቅ የውድድር መድረኮች የምትወከልበት እንዲሆን ድጋፍ ያስፈልገዋል::

ፈጣን እንቅስቃሴ በሚፈልገውና የተመልካችን ቀልብ በመስቀል የሚታወቀው ይህ ስፖርት ተዘውታሪ ይሁን እንጂ በሚፈለገው ልክ ተወዳዳሪዎችን በማፍራት ረገድ ጥረቶችን ማድረግ ይጠበቅበታል:: በዚህም ታዳጊዎች ላይ መሠረት አድርጎ መሥራት፣ ክለቦችን ማቋቋም፣ ማህበራትን ማደራጀት እና ባለሙያዎችን አሰልጥኖና አብቅቶ ጠንካራና ተፎካካሪና ስፖርተኞችን እንዲያፈሩ ለማስቻል መትጋት እንዳለበት ባለሙያዎች ይናገራሉ:: በተጨማሪም ስፖርቱን ለመደገፍ ከሌሎች ደጋፊ አካላት ጋር ሀብት የማፈላለግ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን የቴክኒክ ባለሙያ ብሩክታዊት ተገኝ ገልጸዋል::

በስፖርቱ ተተኪዎችን ለማፍራት በሚደረገው ተግባርም በየክልሉ 78 የሚሆኑ የታዳጊ ወጣት ፕሮጀክቶችን ስልጠና ጣቢያዎችን በማቋቋም ወደ ሥራ ገብተዋል:: በእነዚህ የስልጠና ጣቢያዎች የሚገኙትን አሰልጣኞችም በማሰልጠን በክህሎትና በተግባር የማብቃት ሥራ መሥራት ተችሏል:: ከፕሮጀክት የሚያድጉ ወጣቶችን የሚቀበሉ ከስድስት በላይ ክለቦች በኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ስር ይገኛሉ:: በየካቲት ወር 2015 ዓ.ም የክለቦች ቻምፒዮና የተከናወነ ቢሆንም፤ የክለቦቹ ቁጥር ግን በቂ አለመሆኑ ታይቷል::

ከውድድሩ ብሔራዊ ቡድንን የሚወክሉ ስፖርተኞች ተመርጠው ጅቡቲ ላይ በተደረገ ውድድር በመካፈል ጥሩ ውጤት በማስመዝገብ መመለሳቸውንም ባለሙያዋ ይጠቁማሉ:: በቅርቡ በሚካሄድ ሌላ ውድድር ላይም ይህንኑ ውጤታማነት አስጠብቆ ለመመለስ ታቅዷል:: ከመጪው ግንቦት 23-25/2015 ዓ.ም የሚካሄደው ውድድሩ የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ክለቦች ቻምፒዮና ሲሆን፤ አዘጋጇም ኬንያ ናት:: በኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ የክለቦች ቻምፒዮና የውድድሩ አሸናፊ የሆነው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክም አገሩን በመወከል በቻምፒዮናው የሚሳተፍ ክለብ ይሆናል:: በስፖርቱ የተሻለ የውጤታማነት ታሪክ ያለው ክለቡ በውድድሩ በሚኖረው ቆይታ ውጤት እንደሚያስመዘግብም ይጠበቃል::

በመጪው ዓመት መስከረም ወር 2016 ዓ.ም የአፍሪካ ቻምፒዮና በቱኒዝያ አዘጋጅነት ይካሄዳል:: በዚህም ኢትዮጵያ በወንድ፣ በሴት፣ በነጠላ እና በቡድን መሳተፏን አረጋግጣለች:: ለተሳትፎውም ከሌሎች አካላትና ከመንግሥት ድጋፍ ይጠበቃል:: እስከ አሁን ባለው ሂደት መንግሥት የሚያደርገው ድጋፍ እንደሌሎች የስፖርት ዓይነቶች አጥጋቢ አይደለም:: በተለይ ለቤት ውስጥ ስፖርቶች የሚሰጠው ትኩረትና ድጋፍ በቂ የሚባል አለመሆኑን ባለሙያዋ ያነሳሉ:: በተገቢው መንገድ እንቅስቃሴ ቢደረግ ተወዳዳሪዎች በዓለም አቀፍ ውድድሮች መሳተፍ ቢችሉ ውጤታማ መሆናቸው ግልጽ ነው::

በእርግጥ በጠረጴዛ ቴኒስ ብሔራዊ ቡድኑን የሚወክሉ ተጫዋቾች በቁጥር አናሳ ቢሆኑም ጠንካራና ተፎካካሪ ናቸው:: ነገር ግን እንደ ሌሎች ስፖርቶች ባለማደጉና ትኩረትን መሳብ ባለመቻሉ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ለመሳተፍ አዳጋች እየሆነ መጥቷል:: ስፖርተኞች ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተው፤ ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብ ባክኖ በመጨረሻ ድጋፍ ባለመገኘቱ ተሳትፎን ማድረግ ሳይቻል ይቀራል:: በመሆኑም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ለመሳተፍ ተገቢው ድጋፍ መደረግ እንደሚኖርበት ባለሙያዋ ያሳስባሉ::

በኢትዮጵያ የጠረጴዛ ቴኒስ ተጫዋቾች በቴክኒክ ጥሩ ደረጃ እንደሚገኙ ባለሙያዋ ያስረዳሉ:: በአውሮፓ አገራት ከሚጫወቱ አፍሪካውያን ተጫዋቾች ጋር ጥሩ ተፎካካሪ መሆን የሚችሉ ናቸው:: ይሁንና ፌዴሬሽኑ የስፖርት ቁሳቁስ ችግሮች አሉበት:: ተጫዋቾች የሚጠቀሙባቸው ጠረጴዛ፣ ኳስ እና ራኬት ከሌሎች አንጻር ኋላ ቀር የሚባል ነው:: ደረጃቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸውም በስልጠና ሂደቱ ተጽዕኖ ማሳረፍ ችለዋል:: እንደ አገር ዘመናዊ የስልጠናና ውድድር መሣሪያዎችን ማሟላት ቢቻል ከዚህም የበለጠ ውጤትን ማስመዝገብ ይቻላል:: ሌላው ተጫዋቾች በቴክኒክ የተሻሉ ቢሆኑም በአካል ብቃት ረገድ ግን ደከም ስለሚሉ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል:: በቀጣይም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ በታክቲክና ቴክኒክ ከሚያሰለጥን ባለሙያ በተጨማሪ በአካል ብቃት የሚያሰለጥን ባለሙያ ለመቅጠር እቅድ መያዙንም አብራርተዋል:: ስፖርቱን ለማሳደግና ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ በሚደረገው ጥረትም ፌዴሬሽኑ የባለድርሻ እና የደጋፊ አካላትን እገዛ ይፈልጋል::


## ብሔራዊ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር አአከአድ/ኀባ/ግጨ/01/2015/2023

የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 74/2014 ሸገር የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት እና አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅትን በአንድ በማዋሃድ የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ድርጅቱ በሰንጠረዡ የተገለፁ የተሽከርካሪ ጎማ እና ባትሪ በሀገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሚገዛበት ዕቃ/አገልግሎት | የሎት ምድብ | የጨረታ ማስከበሪያ መጠን | የጨረታ ሰነድ መመለሻ ቀን | የጨረታ ሰነድ መክፈቻ ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአውቶቡስ ጎማ 295/80R 22.5-RR 18 | ሎት አንድ | ብር 400,000 | ሚያዝያ 30/2015 ዓ.ም ጠዋት 4፡00 | ሚያዝያ 30/2015 ዓ.ም ጠዋት 4፡30 |
| 2 | የአውቶቡስ ባትሪ 195-200Amh | ሎት ሁለት | ብር 150,000 | | |
| 3 | የመኪና ጎማ 215/75R17.5-16PR | ሎት ሦስት | ብር 50,000 | | |

ስለሆነም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች፤

1. ከስራው ጋር አገባብነት ያለው ሆኖ በዘመኑ የታደሰ ሕጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የዘመኑን ግብር መክፈላቸውንና በጨረታ መሳተፍ የሚያስችል ወቅታዊ ደብዳቤ (Tax Clearance)፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት (VAT Registration) እና የግብር ከፋይ መለያ ሰርተፍኬት (VAT Certificate) ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ/ በመያዝ 22 እየሩስ ህንጻ 7ኛ ፎቅ የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት የግብአት አቅርቦት አስተዳደር ዳይክቶሬት ቢሮ ቁጥር 7-07 በመምጣት መውሰድ የሚችሉ ሆኖ የጨረታውን ሰነድም በዚሁ አድራሻ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች በሰንጠረዡ በተገለፀው የብር መጠን የጨረታ ማስከበሪያ ከሕጋዊነት ማረጋገጫ ከቴክኒካል /ኦሪጅናል ሰነዶች ጋር በሲፒኦ ወይንም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በማስያዝ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከወሰዱበት ቀን ጀምሮ በተራ ቁጥር 2 በተገለፀው አድራሻ ከላይ በሰንጠረዥ በተገለፀው ቀን ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታ ሰነዱ የሚከፈት ሲሆን ዘግይተው የቀረቡ የጨረታ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
5. ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ለእያንዳንዳቸው ሎቶች የታሸገ አራት ኤንቨሎፕ ቴክኒካል ሰነድ ኦሪጅናል በአንድ ፖስታ፣ ፋይናንሻል ሰነድ ኦሪጅናል በአንድ ፖስታ፣ ቴክኒካል ሰነድ ኮፒ በአንድ ፖስታ እና ፋይናንሻል ሰነድ ኮፒ በአንድ ፖስታ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ኦሪጅናልና ኮፒ ተብሎ ፖስታዎቹ ላይ መገለፅ አለበት፡፡
6. ድርጅታችን ጨረታውን በከፊልም ሆነ መሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ጨረታውን የሚመለከት መረጃ በስ.ቁ 0118639877/0118212282 ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት**



## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 114 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0039806424 ህይወት ተፈራ ገበየሁ ከተመዘገብኩበት አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 0251 እስከ 0253 የተሰራበት እና ከቁጥር 0254 እስከ 300 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ህይወት ተፈራ ገበየሁ**



## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- ባይሊ ፉድ ፕሮሰሲግ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 08 የቤት ቁጥር አዲስ, ሰበታ ኦሮሚያ, ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/14040/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 18/07/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡ | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡-(yummy snack and Image of food honey flavour) |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 30 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ስናክ ማምረት (ምድብ 30) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ሕግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXII No-233 23/8/2015 (1/5/2023)